~📚Course – Social Anthropology

📓Chapter one – Introducing Anthropology and Its Subject Matter

በዚህ ቻፕተር ስር ዘርዘር አድርገን የምናየው የሚከተሉትን ነገሮች።

📌Scope of Anthropology – የአንትሮፖሎጂ ምንነት – Definition, ስፋት – scope ማለትም ምን ምን ነገሮች በውስጡ እንደሚያካትት እንዲሁም "subject matter of Anthropology" ይህ ማለት ደግሞ አንትሮፖሎጂን እንደ ርዕስ ካነሳን ከሱ ጋር በተያያዘ ምን ምንድነው ልናነሳ የምንችለውን ማየት ነው ለምሳሌ ስለ ሰው ልጅ የቀለም ልዩነት👩🟫 👧🧒እያጠናን ከሆነ "Subject"ኡ ላይ ትኩረት አድርገን የሰው ልጅ እራሱ ምንድነው የሚለውን ማጥናት ነው።
📌Branches of Anthropology – አንትሮፖሎጂ በስንት እንደሚከፈልና እነሱን በዝርዝር ማየት 📌Unique features of Anthropology – አንትሮፖሎጂን ከሌሎች የትምህርት ዘርፎች ለየት የሚያረገው ነገር ምንድነው የሚለውን 📌Misconceptions about Anthropology – ሰዎች ስለ አንትሮፖሎጂ ያላቸውን የተሳሳቱ አመለካከቶች እናያለን። 📌 The Relationships between Anthropology and Other Disciplines and Its Contributions – አንትሮፖሎጂ ከሌሎች ሳይንሶች ጋር ያለው ቁርኝት ምንድነው፣ የሚለየውስ አንድ የሚያደርገው ነገርስ ምንድነው የሚለውን እንዲሁም አንትሮፖሎጂ ለሰው ልጅ የእለት ተእለት ኑሮ እንዲሁም ለአለም ያለው ድርሻ ወይም ጥቅም ምንድነው የሚለውን እናያለን🙌

🎯What is Anthropology?

The word anthropology is derived from two Greek Words: 👉"Anthropos" ማለት 'Human being or Man kind👨 ♂👩 🙊- የሰው ልጅ ማለት ነው። 👉 "Logia" ማለት ደግሞ እንደምታውቁት "The Study or Knowledge of" እንደማለት ነው።

So, we can define anthropology, as the systematic study of humankind. "Systematic Study" ማለት ምን ማለት ነው 🤔

"A process of study based on a well-constructed and established foundation."

ስለዚህ አንትሮፖሎጂ ስለ ሰው ልጅ አሳማኝ በሆነ መሰረትና ምክንያታዊነት ላይ ተመስርቶ የሚያጠና ሰብጀክት ነው

ማለት ነው።😄 ነገር ግን ደግሞ አንትሮፖሎጂን ከዚህ በተሻለ መልኩ እንደሚከተለው መግለፅ እንችላለን።

📌Anthropology is the study of human nature, human society, and their behavior; their interactions with each other and with the material environment. ተመልከቱ እዚህ ጋር ስለ ሰው ልጅ ተፈጥሮ – human nature, ስለ ሰው ልጅ ማህበራዊ ኑሮ – human society እና እርስ በእርስ ያላቸው ህብረት ምንድነው የሚለውን እና ከሚታየው ቁሳዊ አለም ጋር ያላቸውን ህብረት የሚያጠና ነው ማለት ነው። እዚህ ጋር ልብ❤️ ስትሉ ሁለት ነገሮች እናስተዉላለን፦👇

"Humans have two essential characteristics – biological and cultural" – ሰውነት የሚባለውን ነገር ካጠናን ስለ ባዮሎጂካዊ ተፈጥሮው እና ስለ ባህሉ የግድ መመልከት አለብን። ከላይ በማብራሪያው "Human nature and human society" እንዳልነው ማለት ነው።

ተመልከቱ ባዮሎጂካዊ ይዘቱ ሄዶ ሄዶ የሰዎ ልጆች ባህላዊ ቁርኝት ላይ ተፅዕኖ እንዴት እንዳመጣ፦ የሰው ልጅ መፈጠር🐣፣ እድገቱ🐥፣ ከዚያ ደግሞ የሰው ልጆች ልዩነት (በዘር፣ በቋንቋ..) ከዚያ የተለያዩ ልዩነቶች ካሉ ደግሞ ህብረት መፍጠር (ባህል) ግድ ነው። ስለዚህ አንትሮፖሎጂ እነዚህን እና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ይዳስሳል።

In more appropriate terms, we can define anthropology as the holistic and comparative study of humanity. 🎯ይህን አሁን ከላይ ያነበባችሁት Definition የሰጠው "Conrad Kottak"👨 🙉የተባለ ሰውዬ ነው። እናም ሁለት ነገሮች በውስጡ ይዟል፦ 1 – Holistic study – ስለ አንትሮፖሎጂ ካጠናን ስለ ሁለንተናው ማጥናት አለብን ማለትም ከላይ እንዳየነው ስለ ባዮሎጂካዊ ይዘቱ፣ ማህበራዊ ህብረቱ፣ ባህሉን እና የመሳሰሉት ማለት ነው። እዚህ ላይ ትኩረት አድርጎ ያጠናው አንትሮፖሎጂስት "James Peacock👨 ♂" ይባላል።

2 – Comparative Study – አንትሮፖሎጂን ካነሳን የተለያዩ ማህበረሰብን ባህል፣ ወግ፣ የቆዳ ቀለም እና የመሳሰሉትን ነገሮች እያወዳደርን ወይም Compare እያደረግን ማጥናት አለብን። እዚህኛው ላይ ደግሞ ትኩረት አድርጎ ያጠናው አንትሮፖሎጂስት "Thomas Eriksen"👴 ይባላል።

"Anthropology shows that many contrasts between men and women arise from cultural learning rather than from biology." ----- Conrad👨 🙉-------

ስለ አንትሮፖሎጂ ምንንትና ጥናቱ እያወራን ስለሆነ ከዚሁ ጋር አያይዘን በሴትና በወንድ መካከል ያሉ ልዩነቶች ማለትም በአቅም፣ በአመለካከት፣ በበላይነት or Dominance እና የመሳሰሉት ነገሮች የመነጨው ከባህል ነው እንጂ በተፈጥሮ አይደለም ይላል። አንትሮፖሎጂ ፌሚኒስት ነው ማለት ነው😁። 🙆 🙆 ♀

አሁንም ቀጥለን የተወሰኑ ስለ አንትሮፖሎጂ Definitions እንመልከት፦ "Anthropology is philosophy with people in." ----Tim Ingold ------ ሰዎች ስለተለያዩ ነገሮች ይፈላሰፋሉ አንትሮፖሎጂ ግን የሰው ልጅ በውስጡ የያዘ ፍልስፍና ነው። ስለ ሰውነት ይፈላሰፋል፣ የተለያዩ ጥያቄዎችን ያስነሳል። ሰውነት ምን ማለት ነው? ሰው በቀለም ✋✋🟫 በቋንቋ🗣️ለምን ተለያየ የሚሉትን ነገሮች ያጠናል።

🎯The major goals of anthropology's investigation of humanity are to understand the uniqueness and diversity of human behavior and human society's around the world. አንትሮፖሎጂ እንዲህ ስለ ሰው ልጆች ወይም ስለ ሰውነት በስፋት ቆፍሮ ማጥናት የተፈለገበት ግቡ የሰውን ልጅ ልዩነት – uniqueness እና በአለም ላይ ያሉ ማህበረሰብና እና የሰው ልጆች ባህሪ ልዩነትና አንድነት ለመረዳት ነው።🙌 📑A Brief History of Anthropology

🎯አንትሮፖሎጂ እንደ "Science or Study of Humanity" መቆጠር የጀመረው በተለምዶ ነገር ግን በስህተት ምዕራባውያን ተብለው ይጠሩ በነበሩት "The West" ፦ France 🇫🇷, Great Britain 🇬🇧, USA 🇺🇸 and Germany 🇩🇪!

አንትሮፖሎጂ ዛሬ የደረሰበት ደረጃ እንዲደርስ የጥንት ሰዎች ብዙ አበርክቷል፣ በተለይ ደግሞ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አካላት ትልቅ ሚና ተጫዉተዋል፦ 🎯 "history of ideas" point of view – የተለያዩ ምሁራን የሀሳብ ልውውጥ 🎯The writings of ancient Greek philosophers and travelers – የጥንት ግሪክ ፈላስፋዎችና ተጓዦች የፃፉት ፅሁፍ ለምሳሌ "Sophists" የተባሉ "group of philosophers" 🎯Medieval Arab historians – የመካከለኛው ዘመን የአረብ ታሪክ አጥኚዎች 🎯Medieval and renaissance European travellers –የአውሮፓ የመካከለኛው ዘመን እና የተሃድሶው🏬 ተጓዦች 🎯 Later European philosophers and social thinkers – ደግሞም የቅርብ ጊዜ (ከመካካለኛው ዘመን👉 ከ5th – 15th) በኃላ ያሉ የአውሮፓ ፈላስፎች እንደነ Michael De Montaigne (16th c), Thomas Hobbes (17th c) and Gimbattista Vico (18th) 🙌ሰዎች ስለ አንትሮፖሎጂ፣ ስለ ስነ ሰው ያጠኑበትን ታሪክ ሞጁሉ ላይ ተንዛዝቶ😫 የተቀመጠውን እዚህ አጠር አድርገን እንመልከት።

በ5th century BC Herodotus👨 🙇‍♂️የተባለ ሰውዬ የሌሎች ሰዎችን ባህል እና ማንነት ለመረዳት ብዙ እየተጓዘ ያጠና ነበር እንዲሁም አወዳድሮ ልዩነታቸውን ያስቀምጥ ነበር።

ከዚያ "Sophists"👴👨 🧔‍♂️👨 🙇‍♂️የተባሉ "group of philosophers" አንፃራዊ እውነታ (relative truth) እንጂ ነባራዊ እውነታ (absolute truth) የለም የሚል ሀሳብ ይዘው መጡ። ልክ እንደዚህ ዘመን ማለት ነው ላንተ እውነት የሆነ ነገር ለኔ ውሸት ሊሆን ይችላል የሚሉ።👀👇

👆ከላይ ያየናቸው ሁለቱም ሀሳቦች እሩቅ መሄድ ሳይችሉ ማለትም በዚያ ዘመን ብዙ ተቀባይነት ሳይኖራቸው ቀርቷል። ምክንያቱም "Herodotus lacked theory while the Sophists lacked empirical evidence [ተጨባጭ ማስረጃ].🙌

ከዚያ Ibn Khalud👨‍🦲 ♂ (1332 – 1402) የተባለ ሰው ደግሞ Emile Durkeim በተባለ ሰው ሀሳብ ላይ ተመስርቶ ማህበራዊ ትስስር (social solidarity) ማለትም የሰዎች ዝምድና እና ሀይማኖታዊ ግኑኝነታቸው አንትሮፖሎጂን ለመግልጽ አስፈላጊ ነው የሚለው ነገር ላይ ነው ትኩረት ያደረገው።

🗣️18ኛው ክፍለ ዘመን የመጨረሻዎቹ አመታት አከባቢ ስለ አንትሮፖሎጂ – ስለ ሰውነት – Humanity – የተለያዩ ጥያቄዎች ተነስተው ነበር። ለምሳሌ፦ Universalism Vs Relativism – Historically Speaking – ለሰዉ ልጆች ሁሉ Common or Universal የሆነ ነገር ምንድነው ❓ የተወሰነው ማህበረሰብ ብቻ ለብቻ ያለው ነገር (Relative የሆነው ነገር) ምንድነው ❓

 Ethnocentrism Vs Cultural Relativism – የሌሎችን ሰዎች ባህል ትክክል ነው ወይም አይደለም ብለን "moral judgement" ማስቀመጥ እንችላለን? ወይስ በአንፃራዊነት ማየት አለብን፥ ለእነሱ ትክክል ሊሆን ይችላል ብለን? Culture Vs Nature – በሰዎች የተገነባውን ባህል መከተል አለብን ወይስ ተፈጥሮን አይተን የተለያዩ በሀይማኖትም ሆነ በፍልስፍና እውነት ነው የተባሉ ነገሮችን መከተል አለብን?

📖Generally speaking, anthropology as an academic discipline was born during the 19th century, out of the intellectual atmosphere of Enlightenment, which is the eighteenth century social philosophical movement.

📑The Enlightenment : a movement of the 18th century that stressed the belief that science and logic give people more knowledge and understanding than tradition and religion. አንትሮፖሎጂ በ19ኛው ክፍለ ዘመን የተወለደው "Enlightenment"💥 በተባለው ሀሳብ ላይ ተመስርቶ ነው። ከላይ እንዳነበባችሁት "Enlightenment" ነገሮችን ሁሉ በባህልና በሃይማኖት ዝምብለን በተረትና በእምነት በማመን ሳይሆን ምክንያታዊነት እና ሳይንስ ላይ ተመስርተን "መግለፅ" አለብን የሚል ሀሳብ ነው። ከ "Darwinian Theory of Evolution" ጋር የሚያመሳስላቸው ነገር አለ። ሀለቱም በ "Logical reasoning – አመክንዮአዊ ምክንያታዊነት" ላይ መመስረታቸው። ቃላቱ ከበድ ከበድ አሉአችሁ አ😅 የተወሰነ ልዩነት ግን አላቸው "Enlightenment idea or philosophy" የሰው ባህሪ ቋሚ ነው (human behavior is constant😶) ይላል ለምሳሌ ሰው ክፉ ከሆነ ወይ መልካም ከሆነ ይህ ባህሪው እንደዚያው ነው የሚቆየው ሊቀየር አይችልም ሲል "Darwinian Theory" ግን ሰው ነፃ ፈቃድ ስላለው ባህሪውን ሊቀይር ይችላል ይላል። ብቻ ያም ሆነ ይህ እኔ የለሁበትም😁 መርሳት የሌለብን ነገር ሁሉቱም ለአንትሮፖሎጂ እድገት ትልቅ ነገር አበርክተዋል።

📌Ethnography is one of the study ways of anthropology in which social and cultural features were studied in detail and documented. 👉 ይህ ማለት ለምሳሌ የሀገራችንን ባህል ማጥናት የፈለገ አንትሮፖሎጂስት👨 💼 መጥቶ በእኛ መካካል እየኖረ፣ ከእኛ ጋር እየበላ እየጠጣ በስፋት – In Detail – ባህላችንን ሲያጠና ማለት ነው። ብዙ ጊዜ የሚታሰበው አንትሮፖሎጂስቶች የ Non – Western world or non – industrialized societies ላይ ብቻ ትኩረት አድርጎ የሚያጠኑ ይመስለናል ነገር ግን አንትሮፖሎጂ የሁሉንም ነው ሚያጠናው።

📌Ethnology is the comparative understanding and analysis of different human groups across time and space. 👉ይህ ደግሞ የተለያዩ ማህበረሰብን👨 👨 👧👫 ባህል እያነፃፀራችሁ በማጥናት✍ "Universal human patterns📜" የባህሎቹ የእድገት ሂደት ወይም የለውጥ ፓተርን እና "The common bio–psychological trait that bind all human beings🐣" – ሁሉንም የሰው ልጆች በ ባዮሎጂውም ማለትም በተፈጥሮም ሆነ በአመለካከት የሚያመሳስላቸው ነገር ምንድነው የሚለውን የምናጠናው በ "Ethnology approach"🔑 ነው።

አሁን ይህን ወደ ማጠቃላያ እናምጣው እስኪ ኡፍ አንትሮፖሎጂ አሁን ያለውን ቅርፅ የያዘው በ20ኛው ክፍለ ዘመን ነው። ለዚህ ደግሞ የሚከተሉት አራት ታላላቅ ምሁራን ትልቅ ሚና ተጫውተዋል⚽።
🧨Franz Boas – USA
🧨Radcliffe Brown – USA
🧨Bronislaw Malinowski – UK
🧨Marcel Mauss – France

🙌እነዚህ "The Founding Fathers of Anthropology" ይባላሉ። መጀመሪያ ላይ አራት ሀገራት አይተን የነበረው አሁን ወደ ሶስት ወርዷል። ጀርመንን አባረሯት😁

📘Subject Matter and Scope of Anthropology

እዚህ ስር ደግሞ አንትሮፖሎጂ እንደ አንድ የጥናት ዘርፍ ወይም "discipline" ምንምን ነገሮችን እንደሚዳስስ እና ይዘቱ – The scope ምን ያህል እንደሆነ አጠር አድርገን እናያለን።

"The discipline touches all aspects of human condition. Wherever human beings live, there is always anthropology."

👉"Anthropology has humanity as its object of research, but unlike the other human sciences, it tries to grasp its object through its most diverse manifestations." ~Claud Lévi–Strauss~

እዚህ ጋር እንደምታዩት አንትሮፖሎጂ ጥናቱ "ሰውነት"ን ወይም "humanity"ን ማዕከል ያደረገ ነው። ነገር ግን ደግሞ ይህን ሲያጠና እንደሌሎች ሳይንሶች በአንድ መንገድ👁ብቻ አይደለም ማለትም ለምሳሌ ባዮሎጂን ብትወስድ ስለ ህይወት ነው የሚያጠናው ጂኦግራፊ ስለ መልከዓ ምድር⛰ ምናምን ሁሉም አንዱ ላይ ትኩረት አድርገው ያጠናሉ አንትሮፖሎጂ ግን ስለ ሰውነት በተለያየ ዳይሜንሽን ባህሉ፣ ማህበራዊ ኑሮው፣ ሀይማኖቱ፣ ፖለቲካዊ ሁኔታ እና በመሳሰሉት መንገዶች።🤌

ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ አንትሮፖሎጂ ሳይንስን መሠረት አድርጎ ነገሮችን እንደሚያጠና አይተናል። የሁለቱን ማለትም የሳይንስና እና የአንትሮፖሎጂን ቁርኝት🤝የሆነ ሰውዬ እንዲህ ገልፆታል፦

"Anthropology is both the most scientific of the humanities and the most humanistic of the sciences" Eric Wolf👨🏻‍🔖ይህ ማለት ሰውነትን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ማጥናት እንዲሁም ሳይንስ እራሱ የተመሰረተው በሰውነት ላይ መሆኑን ሁለቱ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ ናቸው። እንዲሁም "Kluckhohn"👨 🙇የተባለ ሰውዬ አንትሮፖሎጂን እንዲህ ገልፆታል፦ "The science of human similarities and differences"

📑Unique Features of Anthropology

እዚህ ስር የምናየው አንትሮፖሎጂን ከሌላው የትምህርት ዘርፍ ለየት የሚያደርገው ነገሮች ምንድናቸው የሚለውን ነው። እናም የሚከተሉ 4 ነገሮች ልዩ ያደርጉታል አጠር አድርገን በዝርዝር እንመለከታለን። _Its Scope_Its Approach_Its Focus__Its method of study

🎯Broad Scope: አንትሮፖሎጂ ይዘቱ በጣም ሰፊ ነው። ስለ ሰው ልጅ፣ ስለ ባህሉ፣ ስለ ማህበረሰቡ፣ ቋንቋው፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ኑሮአቸው, etc. በጣም ብዙ ቢዘረዘር የማያልቅ ነገሮችን በውስጡ ይዟል።

"No People, place or time is too remote to escape the anthropologist's notice." አያችሁ አይደል ማንም ሰው፣ የትኛውም ቦታ ወይም ጊዜ ከአንትሮፖሎጂ ትኩረት ሊያመልጥ ወይም በጣም ሊደበቅ አይችልም። ያለ ጊዜና ቦታ ገደብ ስለ ሰው ልጆች ሁሉ ያጠናል።

🎯Its Approaches: ይህን ስንል ምን ማለታችን መሰላችሁ አንትሮፖሎጂ በምን አይነት #ዘዴዎች ነው ስለ ሰው ልጅ የሚያጠናው ማለታችን ነው። ስለዚህ እዚህ ስር የሚከተሉ ሶስት ዘዴዎች ወይም "Approaches" እንመለከታለን።🤌

👉Holistic Approach: is an approach in anthropology that it attempt to study a culture or society by

looking at all parts of the system and how those parts are interrelated. 👉ይህ ማለት አንትሮፖሎጂ አንድን "ማህበረሰብ ወይም ባህሉን" በደንብ ለመረዳት በደንብ በስፋት ገብቶበት ከማህበረሰቡና ከባህላቸው ጋር ተያያዥ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ ማጥናት አለበት። ለምሳሌ ታሪካቸውን፣ ቋንቋቸውን እና የመሳሰሉትን። የ ጉራጌን ብሔረሰብ ባህል እናጥና ካልን ሁለንትናውን፣ በደንብ ገብተንበት ባህላቸው ከቋንቋ፣ ከኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ጋር፣ ከታሪካቸው ጋር ያለው "Connections and Interrelationships" ምንድነው ብለን ማጥናት ያስፈልጋል።

👉Relativistic Approach: this approach assumes that societies or cultures have their own unique inner logic and therefore, must be viewed in their context rather than from others point if view. 👉ከላይ አይተን እንደነበረው አንትሮፖሎጂ አንድን "ማህበረሰብ ወይም ባህሉን" ሲያጠና ከሌላው ጋር እያወዳደር ጥሩ ነው ወይም መጥፎ ነው ብሎ ለመፈረጅ #ሳይሆን በራሳቸው "አውድ – context" ውስጥ ሆኖ ይህ ማለት ለእነሱ ምንድነው፣ ይህን ሲያደርጉ ለእነሱ ምን ትርጉም ይሰጣቸዋል? እያለ የሚያጠና ነው። በዚህም አንትሮፖሎጂ የ "Ethnocentrism" ተቃራኒ እንደሆነ እንመለከታለን። "Ethnocentrism" ማለት አንድን ባህል ከሌላው አንፃር አይቶ "🧒⚖️Judge " ማድረግ ነው።

👉Comparative Approach: anthropology is a comparative science that offers a unique, cross-cultural perspective; constantly comparing the customs of one society with those of others. 👉ልብ በሉ ከላይ "Relativistic approach" ላይ ስናይ "እያወዳደር Judge አያደርግም" ነው እንጂ ያልነው አያወዳድርም አይደለም። አንትሮፖሎጂ አንዱ የሚከተለው ዘዴ/ Approach የተለያዩ ማህበረሰቦች ባህል እያወዳደር ልዩነታቸውን እና አንድነታቸውን ማስቀመጥ ነው።

🎯Emphasis on Insider Perspective: Anthropology gives its emphasis on the perspective of an #insider, when examining other culture. 👉ከላይ አንትሮፖሎጂ ልዩ ወይም Unique የሚሆንበትን ሁለት ነገሮች አይተናል "Its Scope እና Its Approach" አሁን ሶስተኛ ላይ የምናየው ደግሞ "Its Focus/Emphasis" ነው። እናም አንትሮፖሎጂ የማህበረሰቡን ባህል ሲያጠና ትኩረቱ በሁለት መንገድ ሊሆን ይችላል። አንድ እዚያው ማህበረሰቡ ላይ ትኩረት አድርጎ፣ እነሱ ስለራሳቸው ባላቸው አመለካከት ላይ ተመስርቶ ሲሆን ሁለተኛው መንገድ ደግሞ አንትሮፖሎጂስቶች እራሳቸው ስለ ማህበረሰቡ የራሳቸውን አመለካከት ሲያስቀምጡ ማለት ነው። 🙌አንትሮፖሎጂ የሚጠቀመው የመጀመሪያውን የትኩረት መንገድ ነው። የመጀመሪያው "Emic🥰Perspective" ይባላል። ሁለተኛው "Etic Perspective" ይባላል።

 Emic Perspective: refers to insider view, which seeks to describe culture or social behavior in terms of the categories, concepts and perceptions of the people being studied. 👉ከላይ በጥቂቱ እንደዳሰስነው፥ የዚያው ማህበረሰብ ሰዎች አመለካከት ላይ የሚያተኩር ነው። ለምሳሌ የደቡብ ኦሞ (ከንፈራቸውን የሚቀዱት🙈) አንድ አንትሮፖሎጂስት ስለነዚህ ህዝቦች ማጥናት ከፈለገ የሚያተኩረው "እነሱ እንደዚያ ሲያደርጉ ለራሳቸው ካላቸው አመለካከት – Insider view" ላይ ነው። በአጭር አገላለጽ "እነሱን ለመግለፅ የራሳቸውን ቋንቋ መጠቀም።" ቋንቋ ሲባል ደግሞ የምር የነሱ ቋንቋ ሳይሆን😁 አውዳቸውን or Their context ለማለት ነው።

 Etic Perspective: refers to outsider view, in which anthropologists use their own categories and concepts to describe the culture under analysis. 👇ይህ ዘዴ ደግሞ አንትሮፖሎጂስቶች ሊያጠኑ የሄዱበትን ማህበረሰብ፣ ባህል በራሳቸው ቋንቋ ሲያብራሩት ማለት ነው። በቀላል ምሳሌ አንተ ጓደኛህን እንዴት ትገልፀዋለህ?🤔 ብትባል ጥያቄውን ከመመለስህ በፊት ሁለት የትኩረት መንገድ አለ። አንድ ጓደኛህ እራሱ እራሱን በሚገልፅበት መንገድ እሱን መግለፅ ሁለት አንተ በራስህ መንገድ እሱን መግለፅ🙌 የመጀመሪያው "Emic" ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ "Etic" ነው። አሁን በድጋሚ አንትሮፖሎጂ የመጀመሪያውን – Insider view perspective – emic ነው የሚጠቀመው። እንዲህ ነው ፈትፍቶ ማጉረስ😁

🎯Method of Research: Anthropology is highly dependent on qualitative research to understand the meaning behind any human activity. 👇ይህ አራተኛው አንትሮፖሎጂን ልዩ የሚያደርገው ነገር ነው። ስለ ሰው፣ ስለ ማህበረሰብ ወይም ደግሞ ስለ አንድ ባህል ሲያጠና "In-depth" ገብቶበት ነው። ዝምብሎ ላይ ላዩን ሳይሆን ወይም "quantitative" በሆነ መንገድ ይህን ያክል ባህል አጠናን፣ ልዩነታቸውና አንድነታቸው እንዲህ እንዲህ ነው ብሎ ለማስቀመጥ ሳይሆን በደንብ ገብቶበት፣ ጥራቱ ላይ አተኩሮ ነው የሚያጠናው። ለዚህ ደግሞ የሚጠቀመው አንዱ ዘዴ በላይኛው ፅሁፍ እንዳየነው "Ethnographic fieldwork" ነው። ይህ ማለት ስለ ማህበረሰቡ በስፋት በመቆፈር ማጥናት ማለት ነው።

---------- እስኪ እንጠቅልለው🙌 አንትሮፖሎጂን አራት ነገሮች ወይም በህሪያት ከሌላው ፊልድ ለየት እንደሚያረጉት አይተናል። "Scope" – ሰፊ ነው። "Approach" – ሁለንተናዊ (holistic), በራሳቸው አውድ (Relativistic), አወዳዳሪ (Comparative). "Focus" – ከራሳቸው አንፃር (emic perspective). "Method of Research" – በደንብ ገብቶበት (Ethnographic fieldwork).

~📚Social Anthropology

📒 Chapter One – Continued

📑Misconceptions about anthropology

👇ከትክክለኛ እውቀት ማነስ የተነሳ የተለያዩ ሰዎች ስለ አንትሮፖሎጂ ያላቸውን የተሳሳተ መረዳት እንመልከት፣ ዋናው "Misconception" የአንትሮፖሎጂ የጥናት ነጥቦች ወይም "Area of its study" ነው። የሚከተለውን👇 ተመልከቱ።

🎯Anthropology is limited to the study of "primitive"👴 societies. 👇 ይህ ማለት ከላይ እንደነካካነው "አንትሮፖሎጂ ስለ ጥንት ፍጥረት ወይም ማህበረሰብ #ብቻ ነው የሚያጠናው። ደግሞም ስለ Non-western

societies ወይም በደንብ ስላልሰለጠኑት🪨 ለማጥናት በምዕራባዊያኑ የተመሠረተ ዘርፍ ነው።" የሚል አመለካከት ነው። ነገር ግን ይህ ትክክል አይደለም! አንትሮፖሎጂ ስለ "ጥንት ወይም ስለ ቀደሙት ሰዎች/ነገሮች ወይም ስላላደጉት ማህበረሰብ ብቻ ሳይሆን በአሁን ዘመን ስላሉትም👱‍♂️ የሚያጠና ነው!

🎯Anthropologists only study the rural people and rural areas. 👉ባለፈው ክፍል እንደተማርነው "Scope"ኡ ወይም ይዘቱ በገጠራማ አከባቢ – Rural Areas ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ሰፊና ሁሉን የሚያጠቃልል ነው። ስለ ከተማ ሰዎች – urban Peoples and urban areas📸ጭምር ያጠናል። መረዳት ያለብን ነገር አንትሮፖሎጂ ስለ ከተማም የሚያጠና ንዑስ ክፍል አለው፣ እሱም "Urban Anthropology" ይባላል።

🎯Anthropology is the study or analysis of fossil evidences of the proto-humans like that of Lucy/Dinkeneshe. 👉ይህ ማለት "አንትሮፖሎጂ ስለ ጥንት የሰው ልጅ ፍጥረት ወይም ቅሪት-አካል (fossils) የሚያጠና ነው።" የሚለው አመለካከት ስህተት ነው። ስለ እነዚህም ያጠናል ነገር ግን ደግሞ ስለ ዘመናዊ የሰው ልጅ ፕሪሚቶች ወይም ሰው አሁን ያለውን መልክና ቁመና እንዲኖረው ያደረጉ የቅርብ ጊዜ ተፅዕኖዎች ምንድናቸው? የሚለውንም ጭምር ያጠናል። ነገር ግን ስለ "human Evolution" ብቻ ነው የሚያጠናው ካልን ስህተት ነው።👌

🎯The Purpose of Anthropology is to study in order to keep and preserve communities far from development. 👉ይህ ደግሞ ሌላኛው የተሳሳተ አመለካከት ነው። "አንትሮፖሎጂ ዋና አላማው ማህበረሰቦችን ከእድገት ለማራቅ ነው። ማህበረሰቦች ባህላችን እንደሚገባ እንዳይለማማዱ ጠንቅ ወይም እንቅፋት ይሆንባችኋል።" የሚል ነው። ነገር ይህን ስህተት ነው። አንትሮፖሎጂ ማህበረሰቦች ባህላቸውን እንዲያሳድጉ የሚያበረታታ ነው እንጂ ለእድገት እንቅፋት አይደለም።

👌በዋናነት ሰዎች ያላቸው የተሳሳተ መረዳት እነዚህ ናቸው። ከማወቅ ባሻገር፣ ድንገት ፈተና ላይ ከመጡ ልታጧቸው አይገባም።👌

<< Th Relationship between Anthropology and other Disciplines and Contributions of Anthropology>>

ይህ ክፍል ማንበብም የማያስፈልጋችሁ ርዕስ ነው። ማለትም ወደፊት አንትሮፖሎጂን ለሚያጠና ሰው እንጂ አሁን ላይ ለፈተናም ሆነ ለሌላ ዲፓርትመንት ተማሪ አስፈላጊነቱ ያን ያህል ስላልሆነ፣ እዚህ ላይ ጊዜ አናባክንም።👌

~📚Chapter Two

📑Sub-fields of anthropology

በዚህ ምዕራፍ ስር የምንመለከተው በአንትሮሎጂ ስር የሚገኙ ንዑስ ክፍሎችን or "Branches" ነው። እነሱም አራት ናቸው። እንደሚከተለው በዝርዝር እናያለን።🙌

📊📜There are four major sub-fields:

🎯Archeological Anthropology 🎯Linguistic Anthropology 🎯Socio-Cultural Anthropology 🎯Physical Anthropology

1🟦 Archaeological Anthropology

📌Studies the ways of lives of past peoples by excavating and analysing the material culture/physical remains (artefacts, features and eco-facts) they left behind.

 አርኪኦሎጂ ማለት "Artefacts, Features እና Eco-facts" ተጠቅመን – እነዚህ ሶስቱ ከታች ምን እንደሆኑ ተመልከቱ – ቀድሞ በጥንት ዘመን ይኖሩ የነበሩት ሰዎች አኗኗራቸው ምን ይመስል ነበር የሚለውን መረጃዎችን እየቆፈረ/ኦ😃 የሚያጠና የአንትሮፖሎጂ ክፍል ነው። ይህንንም የሚያደርገው የጥንት ሰዎች ባህል፣ ወግ ምን እንደሚመስል ለማወቅ ነው።

📜"Artefacts" are material remains made and used by the past peoples and that can be removed from the site and taken to the laboratory for further analysis.

👉አያቹአ የጥንት ሰዎች የሚጠቀሙበት እቃዎች ሆነው ነገር ግን ዛሬም ወደ ላብራቶሪ ወስደን ለምርምር ልንጠቀምባቸው የምንችላቸው እቃዎች ናቸው "Artefacts" የሚባሉት። ለምሳሌ፦ Tools (የተለያዩ መሳሪያዎች የሙዚቃ ሊሆኑ ይችላሉ ወይ ደግሞ አልባሳት🧥ወይም ሌሎች የጥንት ሰዎች ይጠቀሙባቸው የነበሩ ዕቃዎች), ornaments (ጌጣጌጦች 💍), arrowheads (የቀስት ጫፎች) , coins (ሳንቲሞች), and fragments of pottery (የሸክላ ቁራሾች), etc.

 "Features" are like artifacts, are made or modified by past people, but they cannot be readily carried away from the site. 🤏"artefact" እና "artifact" ልዩነት የለውም። የመጀመሪያው ብሪቲሽ Spelling ሲሆን ሁለተኛው አሜሪካን ነው።

👉"Features" ማለት በሰው የተሰሩ፣ የቀረፁ እቃዎች ወይም ግንባታዎች ናቸው። እነዚህን ከ "Artefacts" የሚለያቸው "ካሉበት አንስታቿቸው ወደ ላብራቶሪ ምናምን መውሰድ አትችሉም🤦‍♂️።" ለምሳሌ፦ ancient buildings, fireplaces (ለእሳት ማቀጣጠያ የምትሆን ትንሽዬ ክፍል), steles (የተለያየ ነገር የተቀረፀበት ቋሚ ወይም መሬት ላይ የተተከለ ድንጋይ), and postholes(የጥንት ጉድጓዶች)

 "Eco-facts" are nonartefactual, organic and environmental remains such as soil, animal bones, and plant remains that were not made or altered by humans.

👉እነዚህ ዕቃዎች አይደሉም ነገር ግን "Physical remainings" ናቸው ይህ ማለት ሰው ያልፈጠራቸው ሰውም ሊለውጣቸው የማይችል ነገር ግን ሰው የሚጠቀምባቸው ናቸው፣ ከላይ👆 የዘረዘርናቸውን ምሳሌዎች ተመልከቱ አፈር፦ የጥንት አፈር ምን ይመስል ነበር፣ የሰው ልጅ አጥንት፣ ዕፅዋቶች እኔ የመሳሰሉት.

🙌The most important Subfields of Archeology

🚩 Prehistoric archaeology investigates human prehistory and prehistoric cultures.

👉የሚያጠቃልለው ጊዜ "prehistory period" በመባል የሚታወቀው ከዛሬ 6000 አመት በፊት እስከ መጀመሪያው Artifacts (the first stone tools) ማለትም ከ 2.5Million🙋‍♂️ አመት በፊት ያለው ነው።

🚩 Historical Archeology focuses on the cultures of people who used writing and about whom historical documents have been written.

👉ይህ ግን ከ6ሺ አመት ወዲህ ያለውን ፅሁፍ፣ ቋንቋና የመሳሰሉት ነገሮች ከተጀመሩ ወዲህ ያለውን ታሪክ ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው።

🎈 Ethno-Archeology this branch of archeology study material culture of current societies (e.g pottery products) to understand the cultures or life styles of past societies.

👉ይህን ደግሞ እላይ ካየናቸው ሁለት ለየት የሚያደርገው ነገር የጥንት ሰዎችን ባህል ለማወቅ አሁን ያለው ማህበረሰብ ምን እንደሚመስል ያጠናል። ለምሳሌ የጥንት ሰዎች የጡብ አሰራር ዘዴ ለማጥናት አሁን ያለው የጡብ አሰራር ምን ይመስላል የሚለውን ነው የሚያጠናው።

2️⃣ Linguistic Anthropology

🎯Generally focuses on the evolution of languages by studying contemporary human languages as well as those of the past.

ይህ "ቋንቋ" ላይ ትኩረት በማድረግ የሚሰራ የአንትሮፖሎጂ ክፍል ነው። የዘመኑን እና ያለፉትን ማህበረሰብ ቋንቋ አጠቃቀም እንዴት እንደነበር በማጥናት የቋንቋዎች እድገት ምን ይመስላል የሚለው ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው። ትኩረት ሰጥቶ የሚያጠናው ደግሞ "unwritten languages📜" ላይ ነው። ከጥንት ጀምሮ በአፍ ማለትም በመግባባት ብቻ ሰዎች ይጠቀሙበት የነበሩትን፣ ያልተፃፉ የራሳቸው "spelling" ያልተቀመጠላቸው። ▫️ Linguistic Anthropology studies human language as a cultural resource. ማለትም ቋንቋን ስለ ባህል ወይም "Culture" በደንብ ለማወቅ እንደመሳሪያ የምንጠቀምበት መሆኑ ላይ ትኩረት አድርጎ የሚያጠና ነው።

📑It is divided into four👇 distinct branches or areas of research.

👆Structural /Descriptive Linguistics

▫️ Studies the structure of linguistic patterns. It examines sound systems, grammatical systems, and the meanings attached to words.

በቀላሉ "Descriptive linguistic" በጥንት ዘመን ሰዎች ይግባቡበት የነበረውን ቋንቋ በሰዋሰው or Grammar ምቹ እንዲሆነ በማድረግ፤ ሚጨመረውን በመጨመር አንድ ላይ አድርጎ ማስቀመጥ ነው። ስለዚህ አፍ ከፈታንበት ቋንቋ ውጪ ያሉት ቋንቋዎች አብዛኞች በሰዋሰው አወቃቀር ተመሳሳይ ስለሆኑ ለምደዋቸው የዚያን ቋንቋ ማህበረሰብ ባህል ለማጥናት ያን ያህል ከባድ አይሆንም።

/🗂️Grammatical Structure – ሰዋሰዋዊ አወቃቀር ማለት በቀላል ምሳሌ፦ እሷ በሶ በላች ካልን በተመሳሳይ "Structure" ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ጋር ስናዛምድው "She ate Beso" እናም እሷ – She, በላች – ate, የሁለቱ ቋንቋ ሰዋሰው ተቀራራቢ መሆኑን መመልከት እንችላለን። "በላችና በሶ" ጋር ብቻ ነው የሚቀያየረው። ኮበለልንኮ እንመለስ 🧘🏻♂️🧘🏻♂️😅

👇Ethno-linguistics (cultural linguistics) examines the relationship between language and culture.

👉ይህ ደግሞ ትኩረት ያደረገው የሰዎች ቋንቋ አስተሳሰባቸውን🧠፣ አነጋገራቸውን🗣️፣ ድርጊታቸውን በአጠቃላይ ባህላቸውን እንዴት ነው affect ሊያደርግ የሚችለው የሚለው ላይ ነው።

👇Historical linguistics Focuses on the comparison and classifications of different languages to differentiate the historical links between them.

👉ይህ የተለያዩ ቋንቋዎችን ታሪካዊ አመጣጥ ወይም ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዴት እያደጉ እንደመጡ የሚያሳይ ነው። ይህ ደግሞ በቋንቋዎቹ መካከል ያለውን ቁርኝት እንዲሁም በተለያየ ክፍል አድርጎ ለመመደብ እንዲመች ይረዳል። (ለምሳሌ በተለምዶ እንደምናውቀው የሴም ቋንቋዎች፣ የኩሽ ቋንቋዎች 🇪🇹,...)

👇Socio-linguistics: Investigates linguistic variation within a given language and how the use of language defines social groups.

👉ሁሉም ሰው የሚናገረው ቋንቋ አዚህ አለም ላይ የለም! ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ የምናድግበት ቦታ ወይም ማህበረሰብ፣ የቋንቋው accent ወይም ዘዬ እና የመሳሰሉት ነገሮች ናቸው። ስለዚህ ማህበራዊ ህይወትና እና ቋንቋ "Related" መሆናቸውን እንረዳለን።

🗂️Linguistic anthropology generally focuses on the evolution of languages.

3🟦 Socio-Cultural Anthropology

❓ is the largest sub-fields of anthropology. It deals with human society and culture.

👉ይህኛው የአንትሮፖሎጂ ክፍል እንደየ ሀገራቱ በተለያየ ስም ይጠራል። ለምሳሌ በ "North America" - Cultural Anthropology ይባላል። በ "Germany 🇩🇪" ደግሞ - Ethnology ተብሎ ይጠራል። በ "United Kingdom 🇬🇧 እና "Ethiopia" በመሳሰሉት ደግሞ "Social Anthropology" ተብሎ ይጠራል።

 ትኩረት የሚያደርገው ደግሞ "ማህበረሰብ - Society" ምንድነው ❓ "ባህል - Culture" ምንድነው ❓ ባህልን እንዴት ነው የምናጠናው ❓ በሚሉት ላይ ነው።

📌Society - is the group of people who have similar ways of life. 👉ማህበረሰብ ብለን የምንጠራው ተመሳሳይ አይነት የኑሮ ዘዴ ያላቸው ሰዎች ስብስብ ነው። ያው ያደግንበት ስለሆነ እናውቀዋለን። 🙋‍♂️

📌Culture - is a way of life of a group of people. 👉ባህል የምንለው ደግሞ የተወሰኑ ሰዎች " group of people" የአኗኗር ዘዴ ማለት ነው። ስለዚህ ከማህበረሰብ ጋር የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ መሆናቸውን እንመለከታለን።

📝It studies the social, symbolic or nonmaterial (religious, languages, etc) and material (all man made objects) lives of living peoples.

 Socio-cultural anthropologists engage in two aspects of study.

🙌ባለፈው ክፍል በስፋት አይተነው የነበረው "Ethnology" እና "Ethnography" ናቸው። አዲስ ነገር የለውም ለማስታወስ ያክል አጠር አድርገን እንመልከተው።

1 - Ethnography:- በተወሰነ "Community, Culture ወይም Society" ላይ ሰፊ የሆነ ጥናት ስናደርግ ማለት ነው።

👉 የማህበረሰቡ ህዝቦች ባህሪ ምን እንደሚመስል፣ ወግና እሴታቸው ፣በምን እንደሚተዳደሩ፣ የፖለቲካው ሁኔታ፣ ሃይማኖታቸውን በዝርዝር ገብተንበት የምናጠናበት መንገድ "ኤትኖግራፊ" ይባላል።😇 ያዙት ከታች ካለው ጋር እንዳይምታታባችሁ፥ ፈተና ላይ ስለማይቀር።

2 – Ethnology ደግሞ የተለያዩ Culture ወይም Society "Compare" እያደረግን ስናጠና ማለት ነው። 👉የዚህ ዋና ትኩረት ስለ ባህልና ማህበረሰብ አጠቃላይ ምልከታ ለማስቀመጥ እያወዳደርን ልዩነታቸው እና አንድነታቸውን ለማጥናት "ኢትኖሎጂ" የተባለውን የጥናት ዘዴ ነው የምንጠቀመው።

 Indeed, the primary objective of ethnology is to uncover general cultural principles, the "rules" that govern human behavior.

እንደምትረዱት በተለያየ ማህበረሰብ ባህል መካከል ያለውን ሲያጠና መጥፎና ጥሩ ነው ብሎ ለመፈረጅ ሳይሆን ባህሎቹ የሚተዳደሩበት መርህ ወይም "Principle" ምንድነው የሚለውን ምስጢር ለማግኘት ነው። 💃🕺 የሁለቱን ልዩነት አጠር ባለ መልኩ ከታች በፎቶ በቴብል የተቀመጠውን ተመልከቱ።

🙌ስለ Ethnography ነመ Ethnology ልዩነት ከታች የቀረበ diagram አለ ፤ መመልከት ትችላላችሁ።

አሁን ደግሞ Physical Anthropology ን እንማር።

˜📚Anthropology

´📘Physical/Biological Anthropology

📑Physical Anthropology is a branch of anthropology that focuses on biological aspects of human beings. In addition to this, It studies how culture and environment have influenced biological evolution and contemporary human variations.

👉ይህ አራተኛው የአኔትሮፖሎጂ ክፍል ሲሆን፣ ከስሙ እንደምትረዱት ስለ ሰው ልጅ ባዮሎጂካዊ ሁኔታ የሚያጠና ነው። የሰው ልጅ ተፈጥሮው በባህሉ ላይ እንዴት ተፅዕኖ እንዳመጣ እና አሁን ያለው – Contemporary የሰው ልጆች በቋንቋ፣ በቆዳ ቀለምና ✋🏿✋🏻በመሳሰሉት ላይ ያላቸውን ልዩነት የሚያጠና ነው።

ይህ "Physical Anthropology" በስሩ ብዙ ፊልዶችን ይዟል። የተወሰኑት፦ Biological Anthropology, Forensic

Anthropology, Primatology, Paleoanthropology, population genetics and human ecology.

👉There are two major areas of research in physical anthropology. 1 – Human Evolution: research in human evolution shows that the origin of humanity is traced back over 6 million years.

 ይህ የመጀመሪያው የ "Physical Anthropology" የትኩረት ነጥብ ነው። ስለ ሰው ልጅ አመጣጥ ወይም እድገት🏗 ያጠናል ማለት ነው። የሰው ልጅ መፈጠር ወይም "Evolve" ማድረግ ሲያነሳ ደግሞ 6 million አመታት ወደ ኃላ መለስ ማለት አለብን🙋 ♂ ይላል። የሰው ልጅ መገኛ የሆነችውም አፍሪካ፣ ከአፍሪካም ደግሞ ምስራቅ አፍሪካ በተለይም "The Great Rift Valley" ነው። ኢትዮጵያንም ያካትታል ማለት ነው😊። እነ "Lucy👩🟫 🦧"ን እንደምሳሌ መውሰድ ይቻላል።

2 – Modern Human Variation: human biological variations are the result of the cumulative processes of invisible changes occuring in human life. ይህ ደግሞ የ "Physical Anthropology" ሁለተኛው የትኩረት ነጥብ ነው። አሁን ያሉት የሰው ልጆች እንዴት በቋንቋ🗣 በባህል ፣ በቆዳ ቀለም👩 🦳ልዩነት ተፈጠር የሚለው ላይ ትኩረት ያደርጋል። የዚህ ምንጩ ነው ብሎ የሚያስበው ደግሞ በህይወታችን ውስጥ የሚካሄዱ የሚይታዩ (invisible) ነገሮች ተደምረው በአካላችን ላይ ለውጥ ያመጣሉ። ለምሳሌ የምንኖርበት አየር፣ የምንበላው ምግብ እና የመሳሰሉት ተደማምረው በ "gene"አችን ላይ ተፅዕኖ አላቸው። እንደምታውቁት ደግሞ "gene" ከዘር ዘር ይተላለፋል። በእነዚህ ምክንያት የሰው ልጆች ባዮሎጂካል ልዩነት ይታይባቸዋል።

🙌ስለዚህ ከላይ Physical Anthropology ትኩረት የሚያደርገው በሁለቱ ነገሮች ላይ ነው አልን አይደል፥ እነሱም "Human Evolution" እና "Modern human variation" ናቸው ብለናል። ለሁለተኛው ደግሞ ምክንያቱ "genetics" እንደሆነ አይተናል። አሁንም ይቺን ሞጁላችሁ ላይ በተቀመጠ መልኩ ዘርዘር አድርገን እንመልከተው።

📌Human evolution is the study of the gradual processes of simple forms into more differentiated structures in hominid. 👉የሰው ልጅ ከመጀመሪያው ጀምሮ እንዴት እያደገ አሁን ያለበት ደረጃ ላይ እንደደረሰ የሚያጠና ክፍል ነው። ይህም በሁለት ይከፈላል፦

1 – Paleoanthropology ("paleo" means "old") is the study of human biological evolution through the analysis of fossil remains and archaeological records. 🎯ቀድሞ "Record" ተደርገው የተቀመጡትን መረጃዎች በተለይም ፎሲሎችን በመጠቀም ስለ ሰው ልጅ "Evolution" ስናጠና ማለት ነው። Fossils ማለት እንደምታውቁት የጥንት የሰው ልጆች ቅሬታ ነው። እንደ ሉሲ አይነት ማለት ነው። ስለዚህ የጥንቶቹን ቅሬታዎች "biological ancestors " ከአሁኑ ጋር – Modern humans👱 ♂ የሚገናኙት የቱ ጋር ነው የሚለውን ወይም – "Missing link" – Miss የተደረገው ወይም ያልተገኘው የቱ ጋር ነው የሚለውን ለመፈለግ በዚህ መንገድ ነው

የሚያጠናው።

2. Primatology: studies about primates or recent human ancestors to explain human evolution.
🎯ይህ ደግሞ የሰውን ልጅ አፈጣጠር ለመረዳት ስለ ጥንት ቅሪታዎች ማለትም ስለ 🦍ጎሪላዎች እና ቺምፓንዚዎች – የዝንጀሮ አይነት ላይ ትኩረት አድርጎ አናቶሚውን – ማለትም ባዮሎጂካዊ ሁኔታቸውን እና ማህበራዊ ባህሪያቸውን – Their Social Behavior ያጠናል።

📌Human Genetics:- It focuses to examine the genetic materials of an organism such as DNA and RNA.

ይህ ደግሞ ሁለተኛው ከ "Human Evolution" ቀጥሎ የ "Physical Anthropology" የጥናት ክፍል ነው። ትኩረት የሚያደርገው የሰው ልጅ የፊቱ መልክ፣ ቁመናው፣ በአጠቃላይ genetic ነገሩ እንዴት እንደተለያየ እና ለምን እንደዚያ እንደ ሆነ ነው። ስለዚህ የሰው ልጆችንም ሆነ የቺምፓንዚዎችን😁 DNA እና RNA በማጥናት Genetics እንዴት የሰው ልጆች የተለያይ መልክና ቁመት ላይ ተፅዕኖ እንዳመጣ የሚያጠና ክፍል ነው።

📑Evolutionary and Paleo–anthropological perspectives on human origin

ከዚሁ ከ "Physical Anthropology" ርዕስ ሳንወጣ ከላይ የጀመርነውን ሀሳብ ዘርዘር አድርገን እናያለን።

👉Anthropologists today rely on scientific views of evolution in order to explain human origins. ይህ ማለት አንትሮፖሎጂስቶች ስለ ሰው ልጅ አፈጣጠር ለመረዳት በሳይንስ ላይ ነው የሚመሰረቲት እንጂ ሃይማኖታዊ ወይም አፈ ታሪክ አይጠቀሙም ማለት ነው። ለዚህም ደግሞ "Evolution – ዝግመተ ለውጥ" የተባለው ሀሳብ ላይ ነው የሚመሰረቱት።

🎯Evolution is used to describe the cumulative effects of three independent facts.

👉Replication: The fact that life forms have offspring. ሁሉም ነፍስ ያለው ፍጥረት ልጅ አለው። ስለዚህ በተፈጥሮ የመባዛት አቅም አላቸው።

👉Variation: The fact that each offspring is slightly different from its parents and its siblings.

እያንዳንዱ ልጅ ደግሞ ከሌላው ይለያል። ከዘመዶቹ ሊሆን ይችላል፣ ከወንድሞቹ ሊሆን ይችላል። Even መንታ ሆነው እንኳን አንድ ሊሆኑ አይችሉም።🙌

👉Selection: The fact that not all offspring survive, and those that do tend to be the ones best suited to the environment. ነፍስ ካለው ፍጥረት ከሚፈጠረው ልጅ ከአየሩ ጋር የተስማማ ብቻ ነው ሊቀጥል ወይም ሊኖር የሚችለው። አየሩ ያልተስማማው አይቀጥልም።

እንግዲህ "Evolution – ዝግመት ለውጥ" እነዚህን ሶስቱን ሀሳቦች ነው በውስጡ የያዘው።

📸ይባዛሉ_ሁሉም ይለያያሉ_አየሩ የተስማማቸው ብቻ ይቀጥላሉ

አብዛኞቻችን እንደምናውቀው ይህን ሀሳብ በማቀንቀን የሚታወቀው "Charles Darwin"👨 🙇የተባለ ሰውዬ ነው። እሱ በዚህ ላይ ተመስርቶ ሁለት ዋና ዋና "Theory"ዎች መስርቷል።👇

"Natural Selection and Survival of the fittest"

ያው የሁለት ፅንሰ ሀሳብ ከላይኛው የኢቮሉሽን መሰረታዊ ነጥቦች ጋር ተቀራራቢ ነው።

🎯Natural Selection is the mechanism of Evolution by which organisms that are more adapted to their environment are more likely to survive. 👉"Survival of the fittest" ደግሞ ያው ተመሳሳይ ቢሆንም ግን ከ "Natural Selection" Process አንዱ ነው። ከአየሩ ጋር የተመቻችሁ ፍጥረቶች Survive ማድረግ – የኑሮ መቀጠል ላይ ነው ትኩረት የሚያደርገው። ያ ግን (Natural Selection) ሀሳቡ ሰፋ ያለ ነው።

ሰዎች ድሮ ሃይማኖትን ፍራቻ የዳርዊንን ሃሳብ ቢቀበሉም አውጥተው ግን በማህበረሰቡ መካከል አይናገሩም ነበር። ብሎ ብሎ ይሄ የዳርዊን ሃሳብ ለአዲስ ጥናት መሰረት ሆነ። ይህም "የሰው ልጅ የሚኖር ከዚያም እንደ ሌላኛው እንሰሳ ደግሞ "Evolve" የሚያደርግ ወይም የሚሻሻል ነው።🤦 ♂" ለሚለው ሃሳብ ነው።

📑Anthropological Perspectives on Racial Types and Human Physical Variation

አንትሮፖሎጂ በዚህ አለም ላይ ስላሉ የተለያዩ ዘሮች እና ስለ ሰው ልጅ አካላዊ ልዩነት (በቆዳ ቀለምም ሆነ በተክለሰውነት) ምን ይላል ❓ ሁሉም ሰው ለምንድነው አንድ አይነት ያልሆነው ❓ ለዚህም መልስ የምናገኘው ከ "Physical Anthropologists" ነው። እዚህ ስር ደግሞ በስፋት የምናየው የሰው ልጆች በዝግመተ ለውጥ ሂደት ውስጥ እንዴት ከነበሩበት አየር ወይም "Environment" ጋር እንደተላመዱ ነው። ከዚህም የተነሳ ዘር ወይም "race" የሚባል ነገር እንዴት እንደተፈጠረ እናያለን።🙌

🎯Biologically speaking, a race is a group of organisms of the same species that share similar physical attributes and specific geographic regions. ስለዚህ በባዮሎጂው ዘር የሚባለው ነገር ተመሳሳይ አካላዊ ባህሪ ያላቸው ፍጥረቶች ተዋልደው እነሱን የሚመስል ልጅ – Offspring ማስገኘት የሚችሉ እንዲሁም በአንድ አከባቢ የሚኖሩ ናቸው። በዚህ Definition መሠረት የአንድ ዘር ምሳሌ ማግኘት ከባድ ነው። ምክንያቱም ሰው ብንወስድ ለምሳሌ የሰው ዘር ሁሉ አንድ ነው። ከላይ ባየነው definition መሠረት። ነገር ግን የ 🐕ውሾችን ምሳሌ ብንወስድ ሁሉም አንድ ዝርያ ነው ያላቸው – Canis familiaris ግን ደግሞ ቀረብ ብለን ካየን👀 የተለያየ ዘር ነው ያላቸው፦ በአካልም ሆነ ልጃቸው (Their Offsprings) ይለያያሉ። ይህ የመጣው ደግሞ በ "Selective Breeding" ነው። ይህን ዘዴ ባዮሎጂ ላይ ተምራችሁታል።🙈 ውሾች ከ20ሺ አመታት በፊት 🦊ቀበሮ ነበር የሚመስሉት ይባላል። ውሾቹ እንደ ሰው በ "Geographical Adaptation" አይደለም የተለያዩት። የውሾቹ ባዮሎጂካዊ ነው ለዚያ ነው ከላይ ላስቀመጥነው የ "ዘር" ማብራሪያ እንደምሳሌ የወሰድነው።

🎯Adaptation is a process that increases the likelihood of survival of an organism. 👉የኦርጋኒዝሙን በምድር የመኖር ወይም "Survive" የማድረግ እድሉ የሚጨምርበት ሂደት ነው Adaptation ወይም በአማርኛው "መላመድ" የሚባለው። ለምሳሌ እንደሚኖርበት ውሃው Color መልኩን መቀያየር የሚችለው 🐸እንቁራሪት ከሌሎች እንቁራሪቶች ይልቅ አየሩን ወይም ያለበትን ሁኔታ Adapt አድርጎ በአሳ ሳይበላ ብዙ መቆየትና ዘሩን ማስቀጠል ይችላል።

📌Skin color – One of the most human visible characteristics – is a good example of adaptation to a particular environment. 👉"The darkest skin"👩🟫 👨‍🦲🟫 ♂ ያላቸው ሰዎች አብዛኛዉን ጊዜ ሞቃታማ – Tropical zones ወደ ሆኑት ወደ አፍሪካና ኤዥያ ውስጥ ነው የሚኖሩት። 👉"The lightest skin"👩🏻 👨‍🦲🏻 ♂ ደግሞ ወደ "Northern Europe 🇪🇺" ነው የሚኖሩት። እንደ ጠቋቁሮቹ በቂ የፀሃይ ብርሃን አያገኙም እንደሁም ከዚህ የተነሳ ብዙውን ጊዜ ለቆዳ ካንሰር ተጋላጮች ናቸው።

ከዚህ በፊት ታውቁ ይሆናል ነገር ግን የሰው ልጅ Vitamin D የሚያገኘው ከፀሃይ☀️ ብርሃን ነው። እናም እንዳየነው በ Northern Europe አከባቢ ያሉት "lighter skin" ደግሞ በጣም አነስተኛ የፀሃይ ብርሃን ነው የሚያገኙት። የጥንት ሰዎች ከ40ሺ ምናምን አመታት በፊት በ Tropics አከባቢ ነበር የሚኖሩት። ከዚያ ወደ Northern Europe ሲበታተኑ መጀመሪያ ሞቃታማ አየር ውስጥ በቂ የፀሃይ ብርሃን ያገኙ የነበሩት "darker skin"👨🏿 ♀ በቂ የፀሃይ ብርሃን ወደሌለበት (Northern Europe) ሲመጡ በቂ Vitamin D ስላላገኙ Birthrate'አቸው በጣም ቀነሰና እዚያ አከባቢ "lighter skin" Dominate አደረገ። በጥንት አውሮፓ በምርኮ ወደ ሀገሯ ካመጣቻቸው ጥቋቁሮች አንዱ #በእድል ነጭ ሆኖ ከጥቁሩ ከተወለደ እሱ ከሌሎች ከእርሱ ጋር ከተማረኩት ጥቁሮች ይልቅ ብዙ የመኖርና የመውለድ እድል አለው። ገልፅ ነዋ🙌😊

👉Biological Adaptation ሁሌ የሚሆን አይደለም። ጥንት ይሆን እንደነበረው አሁን ይሆናል ማለት ከባድ ነው። ብዙ "Body's Defense Mechanism" ስለተፈጠር የቆዳን ቀለም ማስጠበቅ ይቻላል። ለምሳሌ "Suntan" የነጭ የቆዳ ቀለም ማስጠበቂያ ነው። Suntan ማለት ነጭ ቆዳ በጣም ለብዙ የፀሃይ ብርሃን ሲጋለጥ ወደ ጥቁር ወይም ወደ ቡኒ ቀለም የሚቀየርበት መንገድ ነው። ያንን ደግሞ መከላከል ይቻላል።

ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ባዮሎጂ ውስጥ "Bergmann's Rule" የሚባል አለ። ይህም የሚገልፀው:- " In colder regions, warm-blooded animals will have stockier bodies tham their counterparts from warmer regions, because stockier bodies are more efficient at retaining body heat."

☝ከዚህ የምንረዳው ነገር "ቅዝቃዜ💦 በነገሰበት አከባቢ የሚኖሩ 'Warm -blooded Animals - የሰውነታቸውን ቴምፕሬቸር በየትኛውም አየር ውስጥ አስጠብቀው (retain አድርገው) መኖሩ የሚችሉ እንስሳት ናቸው' እናም በተፈጥሮአቸው እንዲህ የሆኑ እንስሳት ከሌሎች ሞቃታማ ስፍራ ከሚኖሩ እንስሳት ይልቅ ጠንካራ (Stockier) ሰውነት አላቸው። ለዚህ ደግሞ የ በአርክቲክ የሚኖሩትን የ Inuit ህዝቦች መውሰድ አንችላለን። በአንፃሩ ደግሞ በምስራቅ አፍሪካ የሚኖሩ የ Maasai ህዝቦችን ከወሰድን ሰውነታቸው ለየት ይላል፣ የሰውነታቸውን ቴምፕሬቸር ለማስጠበቅ ከሰውነታቸው ብዙ "heat" መልቀቅ (dump ማድረግ) አለባቸው። ሰውነታቸው ሙቀቱን መቋቋም ስለማይችል። ከዚያ የተነሳ ቀጠን💥 ብሎ ረዘም ያለ ሰውነት ነው ያላቸው።

🙌አያችሁ አይደል ባዮሎጂካል ሁኔታው እንዴት ከአየሩ ጋር ተፅዕኖ እንደሚደራረግ፣ በዚህ ውስጥ ነው እንግዲ የሰው ልጆች የሰውነት ቅርፅና ቀለም እየተለያየ የመጣው።

ስለ ሰው ዘር ልዩነት ይህን ያህል ካየን በቂ ነው፣ በእናንተ ደረጃ ከዚህ በላይ ጠልቆ መግባት አስፈላጊ አይደለም።👍

📑What Anthropologists can say for sure about Human Races?

የሚገርማችሁ ነገር ስለ ዘር ጉዳይ ወጥ የሆነ ሁሉም የሚስማማበት ፅንሰ ሀሳብ ወይም ቲዎሪ የለም። ለምሳሌ ኤዥያውያን (ማለትም ቻይና ምናምን የመሳሰሉት) ከአውሮፓውያን ይለያሉ፣ ነገር ግን ደግሞ መሃል ላያ ያሉ (በግማሽ የአውሮፓውያንን ቆዳ ቀለምና ቁመና እንዲሁም ከኤዥያውም ግማሹን የተካፈሉ ሰዎች አሉ።) እነዚህን የት ነው የምንመድባቸው 🤦‍♂️🤔ለምሳሌ የግሪክ ህዝቦች ነጭ ናቸው ወይስ ጥቁር🤔በብዙ ህዝቦች መካከል እንደዚህ አይነት ድብልቅ አለ። ለዚህ ነው ይሄ የዘር ጉዳይ "Grand Illusion" የተባለው፣ ትልቅ ግራ አጋቢ ጉዳይ እንደማለት ነው።

የሰውን ዘር ስንመለከት ከ ባዮሎጂካዊ እና ባህላዊ ሁኔታ አንፃር መመልከት እንዳለብን አንትሮፖሎጂ ይነግረናል።

🧨ሁሉም የሰው ልጅ "Homo Sapiens Sapiens" ዘር ስር የሚመደብ ነው። ስለዚህ ጥቁር፣ ነጭ የሚባል ነገር የለም። ያ ብቻ አይደለም "Female Species, Male Species" ፦ የሴት ዘር የወንድ ዘር የሚባል ነገር የለም። የቆዳ ቀለምና፣ ቁመት፣ ፀጉር ምናምን ልዩነት አለ፥ ነገር ግን ከባዮሎጂው አንፃር ካየን ይሄ ተራ ነገር ነው።👇

"Most Physical Anthropologists consider race as nearly meaningless when applied to humanity. – ከዚህ የተነሳ እነዚህ አንትሮፖሎጂስቶች ስለ ጥቁርና ነጭ የሰው ዘር ከማጥናት ይልቅ ስለ ጥንት "Ancestry – የዘር ግንድ" ላይ ነው ትኩረት የሚያደርጉት።

🧨ሁለተኛ Consider ማድረግ ያለብን ደግሞ ባህላዊ ሁኔታውን ነው። የሰው ልጅ ቋንቋን እንደሚለምደው ሁሉ፣ በየትኛውም ማህበረሰብ የተወለደ ህፃን ልጅ፣ የዚያን ማህረሰብ ወግና ባህሪ ይዞ ያድጋል። ከዚያ የተነሳ ደግሞ እንደዚያ ማህበረሰብ ዘር ሊቆጠር ይችላል። ስለዚህ ከካልቸር አንፃር ዘርን የሚመለከቱት ደግሞ ማንም ሰው የሌላውን ሰው ባህል የራሱ በማድረግ የዚያ ዘር አባል ሊሆን ይችላል ብለው ይላሉ። ስለዚህ የዘር ጉዳይ ከተነሳ ከላይ እንዳልነው "Illusion – ግራ መጋባት" የሚፈጥር ነገር ነው።

📑Human Sociocultural and biological diversity and similarities

What is to be human?

በዚህ ስር የምናየው ስለ ሰው ልጆች እንዲሁም ሰው ስለ መሆን ነው። ሰው👨👩 መሆን ማለት ምን ማለት ነው?😁

📌"Kluckhohn" correctly pointed out: "Anthropology holds up a great mirror to man and lets him look at himself in his infinite variety." ይህ ሰው "አንትሮፖሎጂ ሰው ወደራሱ ዘወር ብሎ ራሱን እንዲመለከት የሚረዳው ሰብጀክት ነው።" ብሏል። እናም በዚህ ርዕስ ስር የምናየው፦

📌What does every human culture do? 📌What things do only some cultures do? 📌Why aren't all human cultures the same? 📌How does humanity change through time?

🙌ለእነዚህና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች መልስ የምናገኘው ሁለት መንገዶችን በመጠቀም ነው።

❣️ Comparative Approach [Cultural Relativism]፦ ይህ ባለፈው እንዳየነው፥ ባህሎችን ስናነፃፅር አንዱ ከሌላው እንደሚበልጥ ለመፈረጅ ወይም 'Judge' ለማድረግ አይደለም። ነገር ግን ይህኛው "Comparative Approach" የሚለው "ባህሎች ለምን እና እንዴት ተለያዩ 🤔 የሚለውን ለመረዳት አንዱን ባህል ከሌላው ጋር እያስተያየን እና እያነፃፀርን ብንመለከተው ይጠቅማናል ነው።

❣️ Evolution ፦ ይህም እንደምታውቅት የዝግመት ለውጥ🦍👨‍🦲 👌👨 🦐ፅንሰ ሀሳብ (Concept) በውስጡ የያዘ ሲሆን የሰው ልጅ ባዮሎጂካል (አካላዊ) ለውጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለወጠ ስለመጣ ያ ነገር ደግሞ በባህሉ ላይ ተፅዕኖ አሳድሯል። እንዴት 🤔

📌Human biology affects human culture; and similarly, human culture affects human biology.

👉ማለትም ለምሳሌ በጊዜ ሂደት የሰዎች "Brain size"🧠እየጨመረ/ እያደገ እንደመጣ ከ"Human Biology" ማረጋገጥ እንችላለን። ያ ነገር ደግሞ የሰው ልጅ አስተዋይ እንዲሆን እንዲሁም በቋንቋ መግባባት ላይ ጎበዝ እንዲሆኑ ረድቷቷል። በዚህ መንገድ ነው የሰው ልጅ ባዮሎጂካል ለውጥ ባህሉና ላይ ተፅዕኖ ያመጣው። በተቃራኒውም ለምሳሌ የከብት፣ የዶሮ እና የመሳሰሉት እንሰሳት እርባታ ያለበት አከባቢ ባህል የሚያድጉ ሰዎች ወተት 🥛፣ እንቁላል ምናምን ስለ ሚያገኙ አካላቸው እንዲሁም አይምሮአቸው ንቁ እንደሚሆን የታወቀ ነው። በዚህም መንገድ ባህል ባዮሎጂካል ለውጥ እንደሚያመጣ መረዳት እንችላለን። ስለዚህ የሰው ልጅ አፈጣጠር እና እድገት የባህልም የባዮሎጂካል ለውጥም በውስጡ የያዘ ነው።

"The change in human brain has brought cultural changes in terms of increased intelligence, language and even the emergence of writing."

🎯This is why anthropologists use the term Biocultural to describe the dual nature of human evolution. Human beings are described as a biocultural animal.

1. Biological and 2. Cultural dimensions.

📖The Biocultural Animal

ስለዚህ ቅድም እንዳልነው የሰው ልጅ እድገት እና ለውጥ የመጣው በሁለቱ ምክንያት ነው። [Biological and Cultural factors]

👉እስኪ ዘርዘር እያደረግን በቀድሞው ዘመን የነበሩት ሰዎች ባህል በሰውነታቸው ላይ እንዴት ባዮሎጂካል ለውጥ እንዳመጣ እንመልከት፦

🥊 በቀድሞው ዘመን የነበሩት ሰዎች ምግብ ለማግኘት እንዲሁም እሳት ለመፍጠር ድንጋይን (Stone tools) ይጠቀሙ ነበር፥ ለዚህ ደግሞ ብዙ ከሰውነታቸው ብዙ ፕሮቲን (ካሎሪ) ያባክኑ ስለነበር ያ ደግሞ በተዘዋዋሪ የሰውነታቸው ግንባታ ወይም 'Anatomy Structure' ላይ ተፅዕኖ ነበረው።

🥊 የተለያዩ አልባሳት ወይም የሽመና ባህል (the use of clothing) በነበረበት አከባቢ ወፈፍራም ልብሶች መሰራታቸው የሰው ልጅ ሰውነት ብርድ እንዲቋቋም አስችሏቿል፥እንጂ የሰው ልጅ በተፈጥሮ እንዲህ አይነት አከባቢ መኖር ለሰውነቱ (For their Body) አመቺ አይደለም። ነገር ግን ሌሎች እንሰሳትን ብንወስድ በተፈጥሮአቸው (ምንም አይነት ባህል (ልብስ መደረብ😁) ሳይስፈልጋቸው እንዲህ አይነት አየር "Arctic Environment" ውስጥ መኖር ይችላሉ።👇

"All other animals can survive mainly through their biology and by relying on instinct (በተፈጥሮአቸው) rather than such cultural information except human being."

ከዚሁ ጋር አያይዘን 'ሰውነት' ምን እንደሆነ እንመልከት🙌

📑Humanity [ሰውነት] is the most common term we use to use refer to human beings. Humanity stands for the human species, a group of life forms with the following characteristics:

📌Bipedalism (walking on two legs)

📌Relatively small teeth for primates of our size ("Primates" ማለት ዝንጀሮ🐵፣ ጦታ፣ የሰው ልጆች፣ የመሳሰሉት ተመሳሳይ ዝርያ ያላቸው እንሰሳት🙈 ናቸው። እናም ከሌሎች 'Primates' አንፃር ትናንሽ ጥርስ ያላቸው ለማለት ነው። 📌 Relatively large brains for primates of our size – ከሌሎች 'Primates' አንፃር ትላልቅ አይምሮ ያላቸው።

📌Using modern language to communicate ideas – የራሳቸው የመግባቢያ ቋንቋ🗣️👥 ያላቸው።

📌Using complex sets of ideas called culture to survive – ብዙ ነገር በውስጡ የያዘ (እሴት (Value), ወግ–ልማድ (norm)– ከዚህ በፊት ያየናቸው) እነዚህን በውስጡ የያዘ ባህል ያላቸው

እንግዲህ አንትሮፖሎጂስቶች እንደሚሉት ከሆነ ከላይ ያሉትን የሚያሟሉት ናቸው #ሰው የሚባለው። እራሳችሁን መርምሩ አንዱን መስፈርት ካላሟላችሁ ሰው አደላችሁም😂። አዬኤ ስብዕና የሌለበት ሰውነትስ ከእንሰሳነት ምን ይለየዋል😑

❣️ Humanity is a general term that does not specify whether you are talking about males👨 ♂, females👩 ♀, adults👨 🧔 or children👦; it simply means our species– Homo sapiens sapiens– at large. ስለዚህ እንደ አንትሮፖሎጂስቶቹ ማብራርያ #ሰው ሲባል የሰውን ዘር – "Homo Sapiens Sapiens" ነው የሚያመለክተው። እኛ ድሮ የተማርነው "Homo Sapiens" ብቻ ነበር። ነገር ግን አዲሱ የሰው ዘር የመጣው ከሁለት ሳፒየንስ ነው። (አዲሱና አሮጌው ተብሎም ተከፍሏል ወይ አትሉኝም😂)

🙌አጠር አድርጌ ላብራራላችሁ "Homo Sapiens" Species (ዘር) ሁለት "Sub–species" አለው። 1. Homo Sapiens Sapiens – Modern Humans የምንባለው እኛ። 2. Homo Sapiens Neanderthals – ከዝንጀሮ ጋር ተቀራራቢነት ያላቸው ሰዎች🙈 (ፎቶአቸውን ጎግል ላይ መመልከት ትችላላችሁ ከ50ሺ አመታት በፊት ምድር ላይ ነበሩ።)

አሁን 'Humanity' ስንል እያልን ያለነው በዚህ ዘመን ያለውን [Homo Sapiens Sapiens]👨 ♂👩 ♀ና የተወሰኑትን ያለፉትን👨 🧔[Homo Sapiens – neanderthals] የሰው ልጆችን ዘር ነው።

Keep in Mind! "Homo Sapiens Sapiens👨 ♂" እና "Homo Sapiens– neanderthals🧔 ♀" ልዩነት አላቸው፥ የመጀመሪያው "Human that are anatomically modern and behaviorally modern", የሁለተኛው ግን በቀድሞ ዘመን የነበሩትን፣ ያልዘመኑትን😁 የሚወክል ነው። ነገር ግን "Homo Sapiens – neanderthals" መቼ (በየትኛው ጊዜ) ወደ "Homo Sapiens – Sapiens" እንደመጡ አይታወቅም፥ ድንገት ነው በቃ ሳይታወቃቸው እየተለወጡ የመጡት😁

ጨረሰናል😰 ይሄኛው ምዕራፍ አዝግ፣ ለመረዳት የማያመች ነበር፣ በተለይ ሞጁሉ የተዘጋጀበት መንገድ😑።
እንደተረዳችሁ ተስፋ አደርጋለሁ🙌

ጥያቄና አስተያይት👇 @Ucan_Scoreebot

©A+ Tutorial Class

˜📚 Social Anthropology #Anthro

˜📚UNIT THREE

📑Human Culture and Ties that Connect Society

🙌በዚህ ቻፕተር ስር በስፋት የምናየው "Culture" በአማርኛ "ባህል" ብለን የምንጠራው ምን እንደሆነ፣ ምን እንዳልሆነ፣ ባህሪያቱ እንዲሁም ተግባሩ (Its Function) ምን እንደሆነ እንዲሁም አንድን ማህበረሰብን ይገነባሉ የሚባሉትን ነገሮች (The building blocks of human society – Marriage, Family and Kinship ወይም ዝምድና) ምን ማለት እንደሆነ በዚህ ምዕራፍ ስር እናጠናለን።

🎯Conceptualizing Culture: What Culture is and What Culture isn't

👉ምናልባት Culture ማለት ምን ማለት ነው ብትባሉ "ባህል" ልትሉ ትችላላችሁ። ባህል ማለትስ ምን ማለት ነው? ብንባል የማንነት መገለጫ😐። ነገር ግን ባህል እንዲህ በቀላሉ አይብራራም! የተለያዩ ምሁር አንትሮፖሎጂስቶች ስለ ባህል የራሳቸውን ማብራርያ አስቀምጠዋል፣ የተመረጡትን እንደሚከተለው እናያለን።

🎯"Culture is the complex whole which includes knowledge, belief, art, morals, law, custom and any other capabilities and habits acquired by man as a member of society" Edward B. Taylor👇

👆ይህኛው ታዋቂና በብዛት ተቀባይነት ያገኘው ማብራሪያ ነው፣ እንዳነበባችሁት ብዙ ነገሮችን በውስጡ ይዟል። ነገር ግን ዋና ሀሳቡ "አንድ ሰው እንደ አንድ የማህበረሰብ አባል ከማህበረሰቡ የሚወርሰው ወይም የሚማረው ችሎታ ወይም ልማድ ነው 'ባህል' ተብሎ የሚጠራው። 🤝ይህ ችሎታ ወይም ልማድ ደግሞ እውቀት፣ እምነት፣ አረት፣ ግብረገብ (Morals), ሕግጋት፣ ትውፊት ወይም ሌሎች ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ።" በእርግጥ ይህን ማብራሪያ መሸምደድ ላያስፈልጋችሁ ይችላል፣ ዋና ሀሳቡንና የሰውየውን ስም ከያዛችሁ በቂ ነው። ፈተና ላይም አልፎ አልፎ

ስለምትመጣ።😋

🎯"Culture is cumulative creation of man" ~Maliniwoski👨~

👆የዚህ ሀሳቡ ደግሞ ባህል የሰው ልጅ ፍጥረት አጠቃላይ ሁኔታ ነው ይላል፣ ማለትም የሰው ልጆች የሚያደርጓቸው ነገሮች፣ የሚያልፉባቸው ሁኔታዎች ምናምን፣ ይህኛው ማብራርያ ትንሽ ሰፋ፣ ከላይ እንዳየነው መንካት ያለበትን ነጥቦች አልነካም።

🎯"Culture is a way of thinking, feeling and believing. It is the group's knowledge stored up for future use." ~Kluckhon👨 ~

👆ይህንም እንደምትረዱት ባህል የሰዎች የአስተሳሰብ፣ የስሜት እንዲሁም የእምነት መንገድ ነው። የሆነ አይነት አመለካከትና እምነት እንዲሁም ስሜት ያላቸው የሰዎች ጥርቅም ያለበትን ነው ማህበረሰብ ብለን የምንጠራው። ደግሞ እንደምታውቁት ባህልና ማህበረሰብ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ናቸው። በተጨማሪ "ባህል የተለያዩ እውቀትና ቅርሶች ወደፊት ይጠቀማሉ ተብለው በሰዎች አይምሮ፣ በመፅሐፍት የተቀመጡበት ነው።" ይላል።🙌

📝Characteristic or Features of Culture

1. Culture Is Shared and Learned

🎯Culture is not transmitted genetically rather; it is acquired through the process of learning.

👉ባህል በዘር አይተላለፍም፣ ነገር ግን በመማር ልታገኙት የምትችሉት ነው።

🎯This process of acquiring culture after we born is called enculturation. ❗ Enculturation is specifically defined as the process by which an individual learns the rules and values of one's Culture.
"ኢንከልቸሬሽን" 👌 አንድን ባህል ለመልመድ የምታልፉበት Process ነው። ለምሳሌ፦ የዚያን ባህል ትውፊቱን፣ ደንቡን ቋንቋውን መልመድ፣ አለባበሱን ማድረግ..

ሌላው ከዚሁ ጋር ተያይዞ ያለው የ Culture Characteristics "Shared" መሆኑ ነው፣ ማለትም Culture Society ውስጥ ባሉት ቢያንስ ሁለት ወይም ሶስት ሰዎች👨 👩 👧 የሚጋሩት መሆን አለበት። እንጂ አንድ ሰው ከመሬት ተነስቶ የራሴ የሆነ አለባበስ ና ቋንቋ🗣️አለኝ ስለዚህ የራሴ #Culture አለኝ ማለት ትክክል አይደለም።🤦‍♂️

2. Culture is Symbolic

📌ባህል በምልክት ሊገለፅ የሚችል መሆን አለበት፣ ለምሳሌ ሌላ ሀገር ሄዳችሁ አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ የለበሰ ሰው 🇪🇹 ስታዩ በፍጥነት ኢትዮጵያዊ😍 እንደሆነ ትገምታላችሁ!

📌Symbol is something verbal or nonverbal, within a particular language or culture that comes to stand for something else.

3. Culture is All Encompassing

📌Culture is the sum total of human creation: intellectual, technical, artistic, physical, and moral!

👉ባህል እንደምናስበው ቀላል ነገር እንዳይመስላችሁ👀፣ ስለ አንድ ህዝብ ባህል እያጠናችሁ ነው ማለት፣ ስለዚያ ህዝብ አስተሳሰብ🧠፣ አነጋገር🗣️፣ ድርጊት👩 🚒 እና የመሳሰሉት ነገሮችንም ማጥናት ይኖርባችኋል።

4. Culture is Integrated

🎯Cultures are not haphazard collections of customs and beliefs. ባህል ቅርፅና መጣጣም ያጣ የትውፊትና የእሴት ውቅር አይደለም። [ከባባድ ቃላት🤦‍♂️😁]

ለምሳሌ፦ የሰው ልጅ አካል ውስጥ ብዙ System አለአ (Respiratory system, Digestive System, Reproductive...ባዮሎጂ ረሳችሁ😄) እነዚህ አንድ ላይ መጥተው ነው አካላችን ጤነኛ ሚሆነው፣ ባህልም ልክ እንዲሁ ነው😃:- እሴቱ፣ ቋንቋው፣ አለባበሱ ምያምን አንድ ላይ Integrated ሆነው ነው ጤነኛ Culture ሚፈጠረው።

5. Culture Can Be Adaptive and Maladaptive

ይሄ ማለት ለምሳሌ፦ የሰው ልጅ ከTechnology💻 ጋር Adapt ማድረጉ (መልመዱ) በብዙ ጠቅሞታል፣ ነገር ግን ደግሞ በዚያው ልክ ብዙ Side effect አለው።[Maladpativeness] ያ መጥፎ ጎኑ ደግሞ ያንን ባህል እንዳንለምድው ሊያደርገን ይችላል።

👉ስለዚህ ባህልም Adapt ካደረጋችሁት ጥቅም የሚኖረው ባሀል ይኖራል፥ ይኖራል ብቻ ሳይሆን አለ። በአንፃሩ ደግሞ አንዳንድ መጥፎ ባሀል ሊኖር ይችላል "Adapt የማይደረግ ወይም በሌላ ስሙ "Maladaptive" የሆነ።"

6. Culture is Dynamic

📌Culture is changing constantly as new ideas and new techniques are added as time passes modifying or changing the old ways.

አየውላችሁ Culture አዳዲስ ሀሳብ እየተጨመረበት በመጣ ቁጥር በየጊዜው ሊቀያየር ወይም ሊታደስ ይችላል። ፈተና ላይ "Static – ቋሚ" ነው ካለ እንዳትሰሙ።🤦‍♀️ ♂

📝Aspects/ Elements of Culture

🎯Two of the most basic aspects of culture are material and nonmaterial culture.

1🟦 Material Culture

🎈Material culture consist of man-made objects such as tools, implements, furniture, automobiles, buildings, dams, roads.. ከስሙ ራሱ እንደምትረዱት የቅርፃቅርፅ፣ የሚታዩት ነገሮች ባህል ነው። እኛ ባህል/Culture የሚመስለን አለባበስና ቋንቋ ምናምን ብቻ ነዋ😔

🎈The physical substance which has been changed and used by man. It includes technical and material equipments. የሰው ልጅ የፈጠራቸውና እራሱ የሰው ልጅ እየቀያየረ ሊጠቀምባቸው የሚችል ናቸው። ወይም "Civilization" ብለን የምንጠራው።

2🟦 Non-Material Culture

🎈Non-material culture consists of the words the people use or the language they speak, the beliefs they hold, values and virtues they cherish, habits they follow. 🎯ይሄ ደግሞ እኛ በተለምዶ የምናውቀው ነው፦ የዚያ ህዝብ አመለካከት፣ ትውፊት፣ ልማዳቸው፣ ቋንቋቸው እና የመሳሰሉት ነገሮቻቸው " Non-material Culture" ነው ሚባለው።

📝Some of the aspects of non-material culture:- (መገለጫዎቹን ደግሞ እንመልከት)

ሁሉም ባህል በአንድነት ያላቸው ነገሮች ወይም መገለጫዎች አራት ናቸው። 👇Symbols, Language, Value and Norms. "አንድ ባህል በምልክት ማለት በ "Symbol" እና በቋንቋ እንዴት እንደሚገለፅ ማስረዳትም አያስፈልግም፣ ከላይ ስላየን፣ ግልፅም ስለሆነ። ስለዚህ የቀሩትን ሁለቱን – Values and Norms እንመልከት።

🎈 Values: are the standards by which member of a society define what is good or bad, beautiful or ugly. Value (እሴት) ማለት ህብረተሰቡ ጥሩ ነው👌 ወይም መጥፎ ነው👎 ብሎ Judge ያደረገው ነገር ነው።

🎈 Beliefs: are basically Assumptions that refer to the acceptance that something exists or is True, especially without proof. Beliefs (እምነት) ደግሞ አንድ ነገር ትክክል/እውነት ሊሆን እንደሚችል አምኖ መቀበል ማለት ነው። ይህ አዲሱ የተሻሻለው ሞጁል ላይ የለም። ከቀድሞ የተወሰደ ነው። ሊጠቅማችሁ ስለሚችል ነው እዚህ ላይ የጨመርኩት።

እስኪ ሁለቱን በምሳሌ እንረዳ፦ ሞጁሉ ላይ የሚገኘው ምሳሌ እንዲህ ይላል፦

"Education is Good" ይሄ የአሜሪካ Society ውስጥ basic ወይም መሠረታዊ #Value ነው።

"Grading is the best way to evaluate Students" ይሄ ደግሞ እምነታቸው ነው። [ይሄ እምነት አይደል መከራ ሚያበላን🤧] 🤙እንቀጥል

🌹 Norms: are ways of behaving that are considered normal in a particular society. "Norm" ማለት ልማድ፣ ትውፊት የምንለው ነገር ነው። ለምሳሌ የበአል የበአል ሰሞን በሬ🐃 እያረዱ🔪 ፣ ቅርጫ እየተከፋፈሉ በአሉን ሚያከብሩት ነገር Social Norm ነው😎

📝Types of Norms (Informal)

1. Folkways: are informal rules and norms that, while not offensive to violate, are expected to be followed. ይህ ማለት ለምሳሌ Taxi ውስጥ ለትልቅ ሰው መቀመጫ ካልለቀቃችሁ👎 ችግር የለውም፣ ማንምም አይፈርድባችሁም፣ ነገር ግን በSocietyው የተለመደው ከትልቅ ሰው ስር መነሳት ነው።

2. Mores [ሞሬስ]: are also informal rules that are not written, but, when violated, result in severe punishments and social sanction upon the individuals. ይህ ደግሞ ለምሳሌ: የህብረተሰቡ አባል ሆናችሁ ብትሰርቁ ወይ ደግሞ ሰው ብትገድሉ ትቀጣላችሁ👊! ህግ ምናምን ስላለ ብቻ አይደለም ነገር ግን እንዲህ አይነቱ ነገርም በSocietyው መካከል የተወገዘ ስለሆነ።

Mores distinguish the difference between right and wrong, while folkways draw a line between right and rude.

📖Cultural Unity and Variations

🤙አንዳንድ Cultural Features በሁሉም Culture ውስጥ ይገኛሉ [Universal], አንድአንዱ ደግሞ በአብዛኛው ውስጥ ይገኛል ነገር ግን በሁሉም አይደለም [General], ሌሎች የባህል መገለጫዎች ደግሞ በተወሰኑ ባህላት ውስጥ ብቻ ነው ሚገኙት [Particular].

ለምሳሌ፣ Exogamy ከአንድ በላይ ሚስት ማግባት በሁሉም ማህበረሰብ ባህል የተከለከለ ነው"ሞጁሉ ነው ያለው😁 እንጂማ ስንት እናውቃለን.. ይሄ አሁን Universality ነው።

ሌላ ደግሞ የሴት ልጅ ግርዛት ለምሳሌ በአብዛኛው የአለማችን Culture ውስጥ የተከለከለ ነው..ይሄ Generality ነው

እና ደግሞ ሌላው የParticular ምሳሌ የሀገራችንን ጋምቤላ ኦሞ አከባቢ ያሉት ህዝቦች አፋቸውን አይታችሁ ታውቃላችሁ የስረኛው ከንፈራቸው ላይ የሆነ ክብ ነገር አድርገውበት ምናምን🙈🙈😁😁

እየገባችሁ ነው🙌

📖Evaluating Cultural Differences

1. Ethnocentrism: refers to the tendency to see the behaviors, beliefs, values, and norms of one's own group as the only right way of living and to judge others by those standards.

👉Ethnocentrism ማለት የኔ ባህል፣ የኔ ሃይማኖት ፣ የኔ አመለካከት ...ይበልጣል ብሎ ማሰብና የሌላው ትክክል እንዳልሆነ Judge ማድረግ (መፈረጅ) ነው። ይህን ለመረዳት እሩቅ መሄድ አይጠበቅባችሁም፥ እዚሁ አገራችን ይህ ክፉ ዘር በሀይማኖት እና በብሔር ሰዎች ሲያባላ ቆይቷል (አሁንም ሳይቀር)።

📌Ethnocentrism is not characteristic only of complex modern societies. [በጥንት ጊዜም የነበረ ነው፥ በቅርብ የጀመር የዘመኑ ችግር አይደለም።]

በነገራችን ላይ, Ethnocentrism ጥቅም አለው፦ " in preserving traditions of one's own culture." [የራሳችሁን ባህል ለማስጠበቅ ይጠቅማል– ሁሌ የኔ ባህል፣ የኔ ሃይማኖት፣ የኔ ባህል ስትሉ – ዋጋ ስለምትሰጡት እና ስለምትጠነቀቁለት የናንት የሆነን ነገር ማቆየት ላይ መጠነኛ ጥቅም አለው። ግን የሚያመጣው ጥፋት የጎላ ነው።]

2. Cultural Relativism

📌States that cultures differ, so that a cultural trait, act, or idea has no meaning but its meaning only within its cultural setting.

🎯ይህ ደግሞ የ "Ethnocentrism" ተቃራኒ ነው። ማለትም የአንድን ሰው ባህል፣ አመለካከት፣ ድርጊት ከእነርሱ እነርሱ ካሉበት Context መመልከት መቻል ነው።

📌"Cultural relativism suspends judgment and views about the behavior of people from the perspective of their own culture."

የማያውቁት ሀገር አይናፍቅም እንደሚባለው😎 የሌላውን ሰው ባህል የእነርሱ ጫማ ውስጥ ገብተን ስናየው ነው እንጂ በሩቁ መፈረጅ ትክክል አይደለም።🤦‍♂️ የእነርሱ ባህል እነሱን ደስ ሊያሰኝ ይችላል ነገር ግን እኛ የእነርሱን ባህል መናቅ የለብንም። Respect For cultural differences😊

ነገር ግን እዚህ ላይ ሰዎች የተለያየ ሀሳብ አላቸው። Cultural Relativism መጥፎ ነው ብለው የሚያምኑም አሉ። አሁን ላይ አያስፈልጋችሁም ግን በዚህ ዘርፍ ብዙ ማጥናት የሚፈልግ📙 "Mirror for Humanity" የሚለውን መፅሐፍ ፈልጎ ቢያነብ፣ ብዙ ሊረዳ ይችላል።

3. Human Rights

🙏መቼስ ይህን እንደገና ባብራራላችሁ ለቀባሪ ማርዳት ይሆንብኛል😁

"The idea of human rights challenges cultural relativism by invoking a realm of justice and morality beyond and superior to the laws and customs of particular countries, cultures, and religions."

እንዴት መሰላችሁ "የሰው መብት ከባህል፣ ከትውፊት ምናምን በላይ ነው።" ለምሳሌ ሰዎችን መግደል፣ ባሪያ ማድረግ፣ ሴቶችን መጨቆን 😓ባህላቸው የሆነ ማህበረሰብ ልክ ቅድም Cultural difference ስለሆነ Respect ማድረግ አለብን እንላለን?? አይሆንም! Humans have the right to not be murdered, injured, or enslaved or imprisoned without charge!

ስለዚህ እንዲህ አይነቱን የሰውን መብት የሚጋፋውን Culture, Condemn እናረጋለን (እንኮንናለን) እንጂ መቻቻል ነው ምናምን ብለን ዝም አንልም፥ የሚል አመለካከት ነው በዚህ ስር የሰፈረው።

ለዛሬ እንደዚህ ካየን በቂ ነው🤌 ቀጣይ "Culture Change" እንዲሁም ሌሎችን እናያለን። ደህና ሰንብቱ🤗፡

ለጥያቄና አስተያየት👇 👇

All rights reserved! ©A+ Tutorial Class

~📚Social Anthropology

📑Culture Change

📌Why and how do cultures change?

🤌ከዚህ በፊት እንዳየነው አብዛኛው ባህል በየጊዜው እየታደሰ "Modify" እየሆነ ይመጣል፣ መለስ ብላችሁም ያለፉትን Society Culture ብታዩ አሁን ካለው ጋር ተመሳሳይ ሆኖ አታገኙትም፣ በቃ በየጊዜው አዲስ ሀሳብ/አመለካከት ሲመጣ ይቀየራል። የባህል መታደስ ሊመጣ የሚችልባቸውን ዋና ዋና 🤝ምክንያቶች እንደሚከተለው እንመልከት።

📑Culture change can occur as a result of the following mechanisms:

🎯Diffusion: The process by which cultural elements are borrowed from another society and incorporated into the culture of the recipient group is called diffusion.

👉በዚህ ትርጉም ውስጥ "Cultural elements" የተባለው ቋንቋ🗣️፣ ልማድ (Value ብለን የተማርነው)፣ እሴት (Norms) እና የመሳሰሉት ነገሮች ከአንዱ ማህበረሰብ ወደ ሌላው ሲሸጋገሩ ነው #Diffusion የሚባለው። እንደውም ካስታወሳችሁ የሃይስኩል ባዮሎጂ ላይ ተምራችሁታል😀። "Diffusion – መተላለፍ እንበለው በአማርኛ" በሚከተሉ መንገዶች ሊፈጠር ይችላል።

📌Diffusion is direct when two cultures trade with, intermarry among, or wage war on one another.
👉 አንዱ ባህል ከሌላው በቀጥታ ሲኮርጅ😁 ማለት ነው። ይህ ማለት ቀጥታ በንግድ ምክንያት ሲገናኙ፣ የአንዱ

ማህበረሰብ ሌላኛውን የመቀላቀል ከሌላው ጋር የመዳቀል👩 🍼 እድል ካለው፣ እንዲሁም በእርስ በእርስ ጦርነት ቀጥታ ባህሉ ሊተላለፍ ይችላል። እናም ከዚያ የተነሳ ያ ባህል ሊታደስ ይችላል።

📌 Diffusion is forced when one culture subjugates another and imposes its customs on the dominated group. 👉ይህ ደግሞ ለምሳሌ በ "Colonization" ስር የነበረው ማህበረሰብ የእነዚያን Colonize ያደረጉትን ወይም "Dominate" የተደረገውን ማህበረሰብ ባህል በግዴታ ሊቀበል ይችላል፥ እናም ከዚህ የተነሳ ባህሉ ላይ ለውጥ ሊፈጠር ይችላል።

📌Diffusion is indirect this happens when items or traits move from group A to group C via group B without any firsthand contact between A and C. 👉ይህን Physics ላይ ጎበዝ የሆኑ በደንብ ይረዱታል "zeroth law of thermodynamics"😃፥ እሺ ተውት። ከስሙ እንደምትረዱት "Indirectly" ማለትም እናንት ቀጥታ ንክኪ ሳይኖራችሁ ሶስተኛ አካል ሆናችሁ እያለ በሁለቱ በ "A" እና "C" መካከል ገብታችሁ ተፅዕኖ ሲደረግባችሁ እንደማለት ነው። ቀለል ያለ ምሳሌ ለመውሰድ ከናኦል👨 👧የተበደራችሁትን ብድር ለእሱ መመለስ ፈልጋችሁ ነገር ግን ቀጥታ ለእሱ መስጠት ካልቻላችሁና ለናቲ👨🟫 👧እንዲሰጥላችሁ ከሰጣችሁት እሱም ብድር የመመለስን ባህሪ በደንብ ያዳብራል። 🙌በዚህ ዘመን የተለያዩ ማህበረሰቦች ባህል እርስ በእርስ ተፅዕኖ የሚደራረጉት "Indirectly" ነው። ዘመኑ የቴክኖሎጂና የሶሻል ሚድያ ስለሆነ፥ ለሌላው የቀረበውን በቀላሉ ማግኘት የምንችልበት ነው።

🎯Acculturation፥ is the exchange of cultural features that results when groups have continuous firsthand contact. 👉ይህ ደግሞ ሁለቱ የ "Society" አካላት #ቀጣይነት ያለው ግንኙት ሲኖራቸው ነው። መጀመሪያ ተገናኝተው ግኑኝነታቸው ካልተቋረጠ ማለት ነው። ይህ ደግሞ በንግድ ልውውጥ ወይም በቅኝ ገዢነት ሊፈጠር ይችላል። በዚህ ምክንያት የሁለቱም ማህበረሰብ ባህል ወይም ከሁለቱ አንዱ ሊለወጥ ይችላል። ይሄኛውን ከላይኛው 👆 "Diffusion" የሚለየው፥ ይሄኛው "ልውውጥ – Exchange" ነው፥ በሌላ መንገድ ቀጣይነት ያለው – Continuous የሆነ ነገር ነው።። ያኛው ግን "ፍሰት" – ከአንዱ ወደ ሌላው ሲፈስ ነው። ቀጣይነት ያለው ላይሆንም ይችላል።🙌

🎯Invention፥ is process by which humans innovate, creatively finding solutions to problems is a third mechanism of cultural change.

👉የተለያዩ ነገሮች "invent" ሲደረጉ ባህል መቀያየሩ የሚታወቅ ነገር ነው። ለምሳሌ በጥንት ዘመን እናንተም እኔም ሳንወለድ እኛ በድንጋይ ነበር እሳት የሚቀጣጠለው😁 ይሄው አሁን በዚህ ዘመን ክብሪት፣ ከዚያ electric ምናምን መጣ። በሌላ ምሳሌ በ "Middle East እና 🇲🇽Mexico" ግብርና የተጀመረ ጊዜ በባህላቸው ላይ ትልቅ ተፅዕኖ አምጥቶ ነበር። ከዚያ "Industrialization" ሲመጣም እንደዚያው ትልቅ ተፅዕኖ እና መታደስ በባህል ላይ አምጥቷል።

🎯Globalization፥ "Encompasses a series of processes, including diffusion and acculturation, working

to promote change in a world in which nations and people are increasingly interlinked and mutually dependent." 👉እንግዲህ ዘመኑ እንደምታውቁት እየዘመነ ነው፣ ሀገራትም ከሀገራት ጋር የራሳቸው የሚያስተዋዉቁትና የሚለዋወጡት ነገሮች ስላሉ ከዚህ የተነሳ ባህላቸው ሊቀየር ይችላል። ምሳሌ ለመውሰድ እሩቅ መሄድ ሳይጠበቅብን ይሄው ይሄ የምዕራባውያኑ ዘመናዊነት ተብዬው ሀገራችንን እየፀናወተው፥ እንዲሁም የእኛን ባህል እየዋጠ የራሱን ደግሞ እያስፋፋ ነው።😭

📑Marriage, Family and Kinship

እነዚህ አሁን ቀጥለን የምናያቸው ነገሮች ከ "ባህል" ጋር ተያያዥ የሆኑ ጉዳዮች ናቸው።

1️⃣ Marriage👩‍❤️‍👨

🎯The term marriage is not an easy terms to define. There is no universally applicable definition of marriage. 👉ጉድኮ ነው! ምን አይነት ዘመን ላይ እንደደረሰን ተመልከቱ፥ አንድ ለሁሉም የሚሰራ የጋብቻ ትርጉም እንኳን የለም። ማለትም ለአንዱ ትክክል የሆነ ትርጉም ለሌላው ትክክል ላይሆን ይችላል ማለት ነው።😔 ያ ብቻ ሳይሆን ጋብቻ በሁሉም ማህበረሰብ ውስጥ የለም። ለምሳሌ [ከሞጁሉ] አንድ Nayar, Southern India ማህበረሰብ አለ፣ እና እዚህ ማህበረሰብ ውስጥ ተጋብቶ፣ ልጅ ወልዶ፣ ቤተሰብ መስርቶ መኖር ሚባል ነገር የለም👩‍♂️። በአንድ Ceremony ላይ ሴቷ👩 🫗አንዱን ሸበላ👨‍♂️ ትይዝና ስነ ስርዓቱን ተካፍለው ሚፈልጉትን አድርገው ከጨረሱ በኃላ ይለያያሉ፣ በቃ ከዚያ በኃላ እሱም አያውቃትም እሷም አታውቀውም።😐አያችሁ እንዲህ አይነትም ማህበረሰብ አለ።

ሌላው የሱዳን የኑዌር ሰዎችን ባህል ብንመለከት፥ የኑዌር ሴት አባቷ ምንም አይነት ወንድ ከሌለው፥ የወለደው ሴቶችን ብቻ ከሆነ። ከሴቶቹ መሃል አንዷ እንደ ወንድ ወይም ባል ሆና ሌላ ሴት ከዉጪ ማግባት ትችላለች። እና ለዚያች ላገባችው ሴት ከሌሎች ወንዶች ጋር እንድትተኛ ትፈቅድላታለች፥ ከዚያ እሷ ለሚወለደው

ልጅ እንደ አባት ትቆጠራለች፥ ማህበረሰቡ የአባቱዋን ዘር እንዳስቀጠለች አድርጎ ይወስዳታል። እንደነዚህ አይነት የሚያስጠሉ🤮የጋብቻ ባህሎችም አሉ ለማለት ነው። ሁሉም ሰው የማይስማማበት እኔ ግን ሁሉ ሰው ሊስማማበት ይገባል ብዬ የማስበው፥ ሞጁሉ ላይም የተቀመጠው የጋብቻ ማብራርያ የሚከተለው ነው።👇

"Marriage is a union between a man and a woman such that the children born to the woman are recognized as legitimate offspring of both partners."

📑Rules of Marriage

🎯Societies have rules that state whom one can and cannot marry. The most common form of prohibition is mating with certain type of kin that are defined by the society as being inappropriate sexual partners. These prohibitions on mating with certain categories of relatives known as incest taboos.

👉"Incest taboo" ማለት በጣም የሚቀራረቡ የስጋ ዝምድና ያላቸው ሰዎች ሲጋቡ ማለት ነው። ለምሳሌ mother–sons – ይህ ማለት እናት ከወንድ ልጆቿ ጋር መጋባት, Father – Daughters – ይህ ማለት አባት ከሴት ልጆቹ ጋር መጋባት and brother–sisters – ወንድምና እህት መጋባት እንዲሁም ዘመዶች እና የመሳሰሉት እንዲህ አይነት ጋብቻ ደግሞ የተከለከለ ነው፥ በፈጣሪም በህብረተሰቡም ዘንድ።😄

📌Marriage is, therefore, a permanent legal union between a man and a woman. It is an important institution without which the society could never be sustained. 👉ስለዚህ ጋብቻ የማህበረሰቡ ህልውና እንዲቀጥል በማድረግ ውስጥ ትልቅ ሚና አለው። ደግሞም አምላክ የፈጠረው ስርዓት ስለሆነ ቅዱስ ነው።😄

📓Mate Selection: Whom Should You Marry?🤔

👉በእርግጥ ይህን በዚህ እድሜ መማራችን ይጠቅማናል። ስለዚህ ማንን እናግባ?😘 ከመሬት ተነስተህ ያማረችህን ሁሉ አገባለሁ ብትል አይሆንም፣ አንቺም እንደዛው። ለጋብቻም ህግና ደንብ አለው።

1. Exogamy: is the rule by which a man👨‍♂️ is not allowed to marry someone👩 from his own social group. 👉ይህኛው በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የምትኖሩ ከሆነ መጋባትን የሚከለክል ህግ ነው። አስባችሁታል ሰፈር ውስጥ አብራችሁ ያደጋችሁትን፣ የምታፈቅራትን ልጅ አታገባም ሲባል🙈😁 ይህኛው ህግ እንደ "incest taboo" ነው የሚወሰደው። ነገር ግን ደሞ ይህ ህግ ጥሩ ነውም ይባላል👇 ።

🎯In fact, there are some definite reasons for which practice of exogamy got approval.
👉የመጀመሪያ በተለይ በድሮ ዘመን (አሁንም በገጠራማ አከባቢ) በአንድ ማህበረሰብ የሚኖሩ ሰዎች Probably የስጋ ዝምድና ሊኖራቸው ይችላል ተብሎ ስለሚታሰብ፣ የአንትን Society ሴት👩 ማግባት፣ እህትን እንደማግባት ነው የሚቆጠረው።

👉Attraction between a male and female gets lost due to close relationship in a small group. አንድን ነገር Adapt ካደረጋችሁት (ከለመዳቹት)፥ ከጊዜ ቆይታ በኃላ እርካታ ላታገኙበት ትችላላችሁ፤ ልክ እንደዚያው በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ካደጋችሁት ሰው ጋር ተጋብቶ ለመኖር እርካታ ላይሰጣችሁ ይችላል።

👉ደግሞም ጋብቻ የተራራቁና የማይተዋወቁ ሰዎችን ሲያገናኝ ነው፥ የበለጠ ኢነርጂና መነቃቃት የሚፈጥረውም የሚባል የተለመደ አባባል አለ። ደግሞም "Exogamy has adaptive value" ይባላል። ማለትም Exogamy አንዱን ባህል እንዲሁም አንድን ሰው ከሌላው ጋር Adapt የማድረግ፣ የማዋሃድ ባህሪ አለው።

2. Endogamy: A rule of endogamy requires individuals to marry within their own group and forbids them to marry outside it. 👉ይህ ደግሞ የ Exogamy ተቃራኒ ነው። ይህ ህግ በተመሳሳይ ማህበረሰብ ወይም ቡድን ውስጥ ያደጉ ሰዎችን እንዲጋቡ የሚመክር ነው።

📌Religious groups such as the Amish, Mormons, Catholics, and Jews have rules of endogamy.

📌Castes in India and Nepal are also endogamous.

👉ይሄኛው በብዙ ሃይማኖትና ባህላት ዘንድ ታዋቂ ይመስለኛል። ለምሳሌ ክርስትናንም💒እስልምናንም🕋ብትወስዱ ከእነሱ ጋር ተመሳሳይ ከሆነው ውጪ ማግባትን አይፈቅዱም። ከእነሱ ሀይማኖት እና ባህል ውጪ ጋብቻን ይከለክላሉ። ከላይ የተጠቀሰውን የህንድና የኔፓልንም ባህል ምሳሌ መውሰድ ይቻላል።

3. Preferential Cousin Marriage: This type of marriage is practiced in one form or another in most of the major regions of the world. There are two types:

📍 Cross Cousin: are children of siblings of the opposite sex. 👉ይህ ማለት "የእናት ወንድም ልጆች እና የአባት እህት ልጆች" ሲጋቡ ማለት ነው። "siblings of opposite sex" – ግራ እንዳያጋባችሁ! siblings ማለት ወንድም ወይም እህት ማለት ነው። እንበልና የ Mr x እናት አለች እንበል፣ ወንድሞቿም አሉ። የ Mr x እናቱ እና ወንድሞቿ siblings (ወንድምና እህት ናቸው።) የወንድሞቿ ልጆች ደግሞ አሉ። ከዚያ ደግሞ የዚያው Mr X አባት አለ። የአባቱ እህቶች ደግሞ አሉ። የእህቶቹ ልጆች ደግሞ አሉ። "opposite sex" የተባለበት ምክንያት "የእናቱ #ወንድሞች እና የአባቱ #እህቶች ስለሆነ ነው።🙌 አሁን ግልፅ ይመስለኛል።

📍 Parallel Cousins: is when marriage takes place between the children of the siblings of the same

sex. 👉ይሄ ማለት ደግሞ "የእናቴ እህት ልጆች እና የአባቴ ወንድም ልጆች" ሲጋቡ ማለት ነው። ገብቶአቹዋላ Parallel ሲል ተመሳሳይ ፆታ ያላቸው ናቸው ሚጋቡት ማለቱ አይደለም፥ ነገር ግን parallel የተባለው በእናት👱‍♀️ እህት👱‍♀️ ♀ እና በአባት👨ወንድም👨ልጆች መካከል መሆኑ ነው። አያችሁ እዚህም ጋር የላይኛውን ምሳሌ ትንሽ ቀይራችሁ ብቻ መውሰድ ትችላላችሁ።

🎯The most common form of preferential cousin marriage is between cross cousins.

4. The Levirate and Sororate

🌹 The Liverate: is the custom where by a widow is expected to marry the brother (or some close male relative) of her dead husband. ይሄኛው "ባሏ የሞተባት ሴት👩 👨የባሏን ወንድም ወይም የቅርብ ዘመድ👱‍♂️ ♂ ስታገባ ማለት ነው።"

🌹 The Sororate: is the custom where by a died women's husband is expected to marry a Sister (or some close female relative) of his died wife. ይሄ ደግሞ "ሚስቱ የሞተችበት ባል👨በሞተችው ሚስቱ ፋንታ የሚስቱን እህት ወይም የቅርብ ዘመድ👱‍♀️ ♀" ሲያገባ ነው።

📑Number of Spouses

ስንት እጮና ይኑረን? ሚለውን እዚህ ስር እናያለን፥ አሁን ነገሩ ወደ እኛ እየመጣ ያለ ይመስላል😁

🔖Monogamy: the marriage of one man to one woman at a time. 👉Maths ላይ One to One ብላችሁ እንደተማራቹት አይነት ነው😁

🔖Polygamy: marriage of a man or woman with two or more mates. Polygamy can be of two types.

📌Polygyny: [ፖሊጂኒ] the marriage of a man to two or more women at a time. 📌Polyandy: [ፖሊያንዲ] the marraige of a woman to two or more men at a time.

ለምሳሌ ቅድም ያየነው "The Sororate" ላይ አንዱ ሚስቱ የሞተችበት ባል እህቷን ካገባት፣ ሁለት ሴቶች👱‍♂️ ♀👱‍♂️ ስላገባ "Sororal Polygyny" ይባላል። የሚገርማችሁ Polygamy "Advantage"/ ጥቅምም አለው ይባላል።🙈 ልጆች ሲበዙ ከእነዚያ መሃል አንዱ አድጎ ሃብታም ከሆነ ለቤተሰቡ ኢኮኖሚ ጥሩ ነው። "ልጅ ሃብት ነው።" የሚለው አስተሳሰብ ማለት ነው። ይህ ግን አጥጋቢ አይደለም😄። ጉዳቱን ካየን ደግሞ በሚስቶች መካከል መቀናናት ሊፈጠር ይችላል (አንዷ በሌላው ስትቀና)😁። ስንጠቅልለው ጋብቻ ሊያሟላቸው የሚችላቸው ነገሮች አሉ፥ ነገር ግን ደግሞ የሚከተሉ ነገሮችን ሁሌ ላያሟላ ይችላል። አንዱ በሌላው ላይ እንዲሰለጥን መብት ላይሰጥ ይችላል፣ አንዱ በሌላው ላይ የንብረትና የወሲባዊ ግኑኝነት ፈቃድ መብት ላይሰጥ ይችላል፥ ማለትም ከባልና ሚስቱ መሃል አንዱ ፆታዊ ግንኙነት አልፈልግም ቢል መብቱ የሚሆንበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል ነው የሚለው። ጋብቻ ለእነዚህና ለመሳሰሉ ነገሮች ዋስትና ላይሆን ይችላል ነው የሚሉት። ሁሌ ግን እንዲህ መሆን ነበረበት። አይመስላችሁም?🤔

📑Economic Consideration of Marriage

እስኪ አሁን ደግሞ በጋብቻ ጊዜ ሊኖሩ ሚችሉ ወጪዎችን እንይ🙈

🧧These may take place either before or after the marriage can be divided into three categories:

1. Bride Wealth 2. Dowry 3. Bride Service 4. Reciprocal Exchange

1. Bride Wealth: is the compensation given upon marriage by the family of the groom🤵to the family of the bride👰. 👉የሙሽራው ቤተሰብ ለሙሽራይቱ ቤተሰብ ካሳ [Compensation] ሲሰጥ ነው። ይመስለኛል "ካሳ" የተባለው ልጃቸውን ስለወሰደ፥ በእሷ ቦታ ምትክ መሆኑ ነው።😄 በተካሄደ ጥናት መሠረት አፍሪካ ውስጥ 82% የሚሆነው ማህበረሰብ የ "Bride wealth" ካሳ ይፈልጋል። አብዛኞቹ 🐘ላምን እንደ ካሳ ይሰጣጣሉ። የ "Bride Wealth" ዋጋ በጨመረ ቁጥር፥ ጋብቻው በጣም ፅኑ ወይም "Stable" ይሆናል ተብሎ ይታመናል😄።

2. Dowry: involves a transfer of goods or money in the opposite direction, from the bride's family to the groom's family. 👉ይሄኛው ወንዶች ሙሽሮችን ይመቻቸዋል😂 ምክንያቱም በተቃራኒ (ከሙሽሪቱዋ ቤተሰብ ለሙሽራው ቤተሰብ የሚሰጥ ስጦታ) ስለሆነ፣ ለነገሩ ለሙሽሮቹኮ ምንም ጥቅም አይኖረውም ምክንያቱም በቤተሰቦቻቸው መካካል የሚደረግ ስለሆነ🤷‍♂️። "Dowry" ብዙ ጊዜ ወንዶች ብርቅዬ በሆኑበት ሀገር እንዲሁም ሴቶች በቤተሰቦቻቸው ላይ እንደ ጫና – burden😄 የሚቆጠሩበት ማህበረሰብ ውስጥ ነው የሚካሄደው። በተጨማሪም ወንዶች በጋብቻቸው ውስጥ ስለሚጠብቃቸው ኃላፊነት ካሳ እንዲሆናቸው ተብሎ ነው፥ ለሙሽራው ቤተሰብ የሚከፈላቸው።

3. Bride Service: is when the groom works for his wife's family. 👉ይህ ደግሞ በመፅሐፍ ቅዱስ📖 ዘፍጥረት ላይ አንብባችሁ ከሆነ ያዕቆብ👱‍♂️ የላባን ልጅ ራሄልን👱‍♀️ ለማግባት ሲል የላባ👨ቤት ውስጥ ለ14 አመት ላባን አገልግሎት ነበር። ስለዚህ Bride Service ማለት ሙሽራው ሙሽራይቱን ለማግባት ቤተሰቧን ሲያግዝ ወይም ሲያገለግል ማለት ነው።

4. Reciprocal Exchange: involves the roughly equal exchange of gifts between the families of both the bride and the groom. 👉ይህ ደግሞ ሁለቱም የሚሸራውም የሙሽራይቱም ቤተሰብ የሚሳተፉበት፥ ቀለል ያለ ስጦታ የሚለዋወጡበት ነው። ስጦታው ብርም💵፣ እቃም🧿፣ እንስሳትም 🐃 ሊሆን ይችላል። በ "Western Kenya", Vugusu የተባለ ማህበረሰብ ይህን አይነቱን ባህል እንደሚከተል ተቀምጧል።

📑Post-Marital Residence

🎯Is where the newly married couple lives after the marriage ritual is governed by cultural rules, which are referred to as post-marital residence rule. 🤦‍♀️ እኔና ሚስቴ ከተጋባን በኃላ የት እንኑር የእነሷ ቤተሰቦች ጋር ወይስ የኔ ቤተሰብ ጋር ወይስ ሌላ ቦታ🤔እነዚህን ያዟቸው👇👇 ፈተና ላይ አይቀሩም!!

📌Patrilocal Residence: the married couple lives with or near the relatives of the husband's father. 👉 የተጋቡት እጮኛሞቹ ከባልየው አባት ቤተሰብ ጋር ሲኖር ማለት ነው።

📌Matrilocal Residence: the married couple lives with or near the relatives of the wife. 👉 የተጋቡት እጮኛሞቹ ከሚስትየው ቤተሰብ ጋር ሲኖሩ ማለት ነው።

📌Avunculocal Residence: The married couple lives with or near the husband's mother's brother. 👉 የተጋቡት እጮኛሞቹ ከባልየው እናት ወንድም ጋር ሲኖሩ ማለት ነው።

📌Ambilocal/Bilocal Residence: The married couple has a choice of living with relatives of the wife or relatives of the husband. 👉 የተጋቡት እጮኛሞቹ ከሚስትየው ወይም ከባልየው ቤተሰብ የፈለጉት ጋር ለመኖር ምርጫ ሲኖራቸው ማለት ነው።

📌Neolocal Residence: The Married couple forms an independent place of residence away from the relatives of either spouse. 👉የተጋቡት እጮኛሞቹ ከራሳቸው ቤተሰብ ርቀው የራሳቸው መኖሪያ ስፍራ ሲኖራቸው ማለት ነው። ብዙዎቻችን የሚመቸን ይሄ ነው😍።

2🟦 FAMILY

🎯Family is the basis of human society. It is the most permanent and most pervasive of all social institutions.

📌Cultural anthropologists have identified two fundamentally different types of family structure.

🎯The Nuclear Family: The nuclear family is generally defined as a family group made up of a married couple and their dependent children. 👉ይሄ "Nuclear family" የሚባለው "Core members of the family" – የቤተሰቡ ወሳኝ ወይም ዋና አባላት ሚባሉትን ሰዎች ብቻ👆 የያዘ ነው፥ ለዚያም ነው ስሙ እንዲህ የተባለው። እንዲህ አይነት ቤተሰብ ብዙ ጊዜ የሚገኘው አሜሪካ፣ ካናዳ የመሳሰሉ፥ ብዙ የሰው ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ መዘዋወር ባለበት አከባቢ ነው። አንድ ቦታ ቋሚ ሆኖ ለብዙ አመታት ላይኖሩ ስለሚችሉ፥ ቀለል ያለ እንዲህ አይነት ቤተሰብ ነው ያላቸው።

🎯የትኛውንም ወጣት ልጅ ከወሰድን የሁለት ቤተሰብ አባል ነው። የመጀመሪያው የተወለደበትና ያደገበት👶 ቤተሰብ ስር ይመደባል፥ "Family of Orientation" ይባላል። ሁለተኛው ደግሞ በጋብቻ ለሚያቋቁመው👨 🍼 የራሱ ቤተሰብ ስር ይመደባል፥ "Family of Procreation" ይባላል።

🎯Extended families: Consist of two or more families that are linked by blood ties. Most commonly, this takes the form of a married couple living with one or more of their married children in a single household🏠. 👉ይህ ደግሞ እንዳነበባችሁት ከአንድ በላይ "nuclear family" አብረው በአንድ ቤት ሲኖሩ ነው። ለምሳሌ የተጋቡ ባልና ሚስት ከባልየው ቤተሰብ ማለትም አባትና እናት ቤት ሄደው የሚኖሩ ከሆነ፥ በዚያ ሰፊ ቤተሰብ ውስጥ የባልየው አባት እንደ አጠቃላይ "family head" ተወስዶ የሚያተዳድርበት አይነት ቤተሰብ ነው። የባልየውም ሚስት በባልየው እናት ቁጥጥር ስር ትሆናለች🙌 📌In the case of a patrilineal extended family, the young couple takes up residence in the homestead of the husband's father and continues to work with his father. 👉ከላይ እንደምሳሌ የወሰድነው እዚህጋም ብንወስደው በጣም አሪፍ ነው። ከዚያ በተጨማሪ ከላይ "Post-Marital Residence" ስናጠና "Patrilocal Residence" አይተን ነበር። እሱም የተጋቡት ባልና ሚስት የባልየው አባት ቤት አንድ ላይ የሚኖሩበት ማለት ነው። ከዚያ እንዳልነው የባልየው አባትና እናት በቤተሰቡ ላይ የበላይ ስልጣን ይኖራቸዋል። ይህም ከዚህ ከ "Extended Family" ጋር ተመሳሳይነት አለው። በእንደዚህ አይነቱ ማህበረሰብ ውስጥ

ጋብቻ ሚስትን እንደማግኘት ብቻ ሳይሆን ልጅን ወደ ቤተሰብ እንደመጨመር ተደርጎ ስለሚታሰብ ነው።🙌 አሁን ቀጥለን የምናየው የጋብቻና የቤተሰብ ተግባር ወይም "Function" ምን እንደሆነ ነው።

📑Functions Marriage and Family

📌 Biological Function: The institution of marriage and family serves biological (sexual and reproductive) function. 👉ጋብቻና ቤተሰብ ውስጥ ከሚኖሩ ስራዎች (ስራ ልበለው መቼስ ሌላ ምን እሏለው😂) መካከል አንዱ ባልና ሚስት የግብረ ስጋ ግኑኝት በመፍጠር የቤተሰቡን ህልውና ማስቀጠል ነው።

📌 Economic Function: Marriage brings economic co-operation between men and women and ensure survival of individuals in a society. 👉ባልና ሚስት አንድ ላይ ሲመጡ በኢኮኖሚ ትልቅ አቅም ይፈጠራል።😇 ድር ቢያብር 🦁አንበሳ ያስር ይላል የሃገሬ ሰው። ስለዚህ ጋብቻና ቤተሰብ ለዚህም ሊጠቅም ይችላል።

📌 Social Function, Educational and Socialization Function, etc 👉በእነዚህም ስር የምናስተውለው ነገር ጋብቻና ቤተሰብ ማህበራዊ ትስስርን እንደሚያጠናክር፣ የተማረ የሰው ኃይል የሚበዛው ከቤተሰብ ነው፥ ወላጆች ልጆቻቸውን ሲያስተምሩ እና የመሳሰሉ ነገሮች ላይ ጋብቻና ቤተሰብ ትልቅ ተፅዕኖ አላቸው።

3️⃣ KINSHIP [ዝምድና]

🎯A kinship system is defined as the network in which people are related to one another through blood, marriage and other ties.

👉ከማብራሪያው ልትረዱ እንደምትችሉት "Kinship" ማለት ዝምድና ማለት ነው። ዝምድናው ደግሞ የተፈጠረው ምናልባት በጋብቻ ወይም ደግሞ በዘር-ማንዘር [descent]፣ ብቻ የሆነ አይነት የስጋ ወይም የዘር ግንኙነት ሲኖር ወይም ደግሞ ከስጋም ዝምድና ውጪ የሆነ አይነት [ባህላዊ ወይም ሌላ] ትስስር ሲኖር "Kinship" ይባላል።

🎯ነገር ግን አሁን ላይ ብዙ አንትሮፖሎጂስቶች ዝምድናን ከደምና ዘር ጋር አያገናኙትም ይልቁኑ ከማህበራዊ እና ባህላዊ ቁርኝት ጋር ነው የሚያያዙት። በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ አንድን ባህል የሚካፈል፣ ለብዙ አመታት አብሮ የኖረን ህዝብ እንደ ዘመድ ያዩታል ወይም "Kinship" ብለው የሚትረጉሙት እንደዚያ ነው። በደም ወይም በዘር ዘመድ የሆኑትን ደግሞ "Kin" ብቻ ይሏቸዋል። በዘር ዘመድ ያልሆኑትን ደግሞ "Non-Kin" ይሏቸዋል።🙌 እስቲ አሁን ደሞ ቀጥለን

ሶስቱን👇 የዝምድና አይነቶችን እንመልከት።

🎯Kinship can be created through three ways: blood, marriage and through adoption/fostering/good-parenthood.

🌹 The relationship based on blood ties [በደም ትስስር ላይ የተመሰረተ ህብረት] is called "Consanguineous Kinship" and the relatives [ሰዎቹ] of this kind is called "Consanguineous kin"፥ ይህ በደም፥ ማለትም ከአየት ወደ አባት ከአባት ወደ ልጅ ከዚያ ወደ ልጅ ልጅ እንዲህ እያለ በደም የሚተላለፍ ወይም የሚፈጠር የዝምድና አይነት ነው።

🌹 በተጨማሪ ደግሞ ሰዎች ለመራባት / ዘራቸው እንዲበዛ (Reproduction) ካላቸው ፍላጎት የተነሳ ይጋባሉ፥ This Kind of Bond, Which arises out of a Socially or legally defined Marital relationship, is Called a "Affinal Relationship" and The Relatives are Called "Affinal Kin"፥ ይህ በጋብቻ ላይ የተመሠረተ ዝምድና ነው። በሚስቱና በባልየው ዘመዶች መካከል የሚፈጠር የዝምድና አይነት ነው።

🌹 ሶስተኛው ደግሞ በ "Adoption – ጉዲፈቻ" የሚፈጠር የዝምድና አይነት ነው። ይህ "Principle of fictitious kinship" ይባላል። "fictitious" ማለት ምናባዊ እንደማለት ነው፥ "real" ያልሆነ ማለት ነው።

4️⃣ DESCENT

🎯A descent group is a permanent social unit whose members claim common ancestry. 👉ዘር ማንዘር የሚባለውን ነገር ታውቁታላችሁ🤔፥ ከአንድ ዘር የመጡ ሰዎች ስብስብ ናቸው "descent group" የሚባሉት። ያው ይህ እኛ አሁን ባለንበት ማህበረሰብ የተለመደ ነው። አንድ የጥንት ዘር ጠቅሶ፥ "እኔ የእከሌ ልጅ ነኝ" ቢል፥ ዘሩን እየመዘዘ መሆኑን ነው የሚያሳየው እናም "descent" የምንለው ያንን ነው። አይነቶቹን ደግሞ እንደሚከተለው እንመለከታለን።🙌

👉There are three important rules of decent are follows:

1. Patrilineal Descent: is When descent is traced solely through the male line. 👉ይህ ማለት ዘርማንዘሩ በወንዱ👨‍🦲 ♂ በኩል ብቻ ሲቀጥል ማለት ነው። ለምሳሌ አንድ አባት👨 🫃ወንድና ሴት ልጆች ካሉት፣ ሴቶቹ ግን ልጅ ወልደው የአባታቸውን ዘር ካላስቀጠሉና ወንድ ልጅ ብቻ ዘሩን ሲያስቀጥል ነው "Patrilineal Descent" ብለን የምንጠራው።

2. Matrilineal Descent: is When the descent is traced solely through the female line. 👇 ይህ ደግሞ ዘሩ በሴቷ ልጅ በኩል ብቻ ሲቀጥል ነው። አባትዋ ለልጀዋ እንደ አያት ሆኖ ለመጠሪያነት ባይሆንም፥ ልጅ👶 ከወለደች የአባቷን ዘር እንዳስቀጠለች መወሰድ ይችላል።

3. Cognatic Descent: Here there is no fixed rule to trace the succession and inheritance ; any combination of lineal link is possible in such societies. 👇ይሄ ደግሞ ዘሩ ወይ በሴቷ ወይ በወንዱ ወይ ደግሞ በሁለቱም ሲቀጥል ነው።

📑Cultural Area and Cultural Contact In Ethiopia

ኮርሱ ጂኦግራፊ መሰላችሁ አደል😁 ፈተና ላይ ስለማይቀር ነው ኖቱን አጠር አድርጌ ያቀረብኩት🙌።

1🟦The Plough [እርሻ] Culture Area 📌Represents those parts of the country where agriculture is predominantly the means by which subsistence is eked out.

📌Most of the highland and central parts of the country is considered as plough culture.

2🟦Enset [እንሰት] Culture Area

📌Covers a vast region in the southern part of the country.

📌SNNPRS regions like Guraghe, Sidama and Gedeo constitute enset culture area.

3🟦Pastoral [እረኝነት] Culture Area

📌Found in the lowland areas covering a large section of the Afar in the northwest, Somali in the

southeast and Borena, these areas inhabitants rely on herds and cattle for living.

📌They usually don't stay in one place. They are not stagnant. Mobility is a major characteristic feature of the people.

ቻፕተር 3 በዚህ መልኩ ጨርሰናል፥ እንቀጥላለን። ደህና ሁኑ🤗፡

ለጥያቄና አስተያይት👇 @Ucan_Scorebot

Your Success is guaranteed with A+! ©A+ Tutorial Class

˜📚CHAPTER FOUR – MARGINALIZED, MINORITIES AND VULNERABLE GROUPS #Anthro

📑Definition of Concepts

መጀመሪያ ከላይ በምዕራፉ ርዕስ ላይ የተዘረዘሩ ርዕሶችን ትርጉም ወይም ምን ማለት እንደሆኑ እንመልከት።

🎯What is marginalization?

˜📝Marginalization is defined as a treatment of a person or social group as minor, insignificant or peripheral. 👉"Marginalization" ማለት #ማውገዝ ማለት ነው። ሰውን ወይም አንድን የማህበረሰብ ግሩፕ በተለያየ ምክንያት እንደ አናሳ – minority ፤ እንደማይጠቅሙ – insignificant እንዲሁም ተጓዳኝ ወይም ተጨማሪ – Peripheral እንደሆኑ በማሰብ (Exclude/Ostrasize ማድረግ) ማለት ነው።

🎯"Marginalization involves exclusion of certain groups from social interactions, marriage relations, sharing food and drinks, and working and living together."

👉ለምሳሌ ያክል በተወሰኑ የኢትዮጵያ ክፍሎች ጡብ ሰሪዎች – Potters እና የእንስሳትን ቆዳ የሚገፉ ወይም የሚፍቁ – Tanners የተወገዙ ናቸው። ስለዚህ እንደዚሁ በተለያዩ ሌሎች ነገሮች ከማህበረሰቡ ጋር እንዳይቀላቀሉ፣ እንዳይበሉ፣ እንዳይጠጡ፣ ህብረት እንዳያደርጉ ይወገዛሉ። አጠቃላይ የአለማችንን ማህበረሰብ ስንመለከት በጣም የሚወገዙት እነማን ይመስሏቸዋል 🤔

🎯Who are mostly marginalized?🤔

ከባህል "diversity" የተነሳ እንደየ ማህበረሰቡ የሚለያየ ነገር ቢሆንም በአለም ዙሪያ ለምሳሌ በጣም የሚወገዙት፥ ብዙዎቻችን እንደምናውቀው 👴ሴቶች፣ 👦ህፃናት፣ በእድሜ የገፉ👴 እንዲሁም አካል ጉዳተኞች🧒 🧑‍🦽 👩 🧑‍🦽 ናቸው።

ከዚያ በተጨማሪ ደግሞ በሃይማኖት፣ በጎሳና በዘር ላይ ተመስርቶ በተለያዩ ማህበረሰቦች የሚወገዙ አሉ።

ከዚያም በተጨማሪ ደግሞ በሙያቸው ላይ ተመስርቶ የሚወገዙ አሉ። ከላይ በምሳሌ እንደወሰድነው በኢትዮጵያ በተወሰኑ አከባቢዎች " Tanners – የእንስሳት ቆዳ #የሚገፉ (አጥብቃችሁ አንብቡት😄), Potters – ጡብ ሰሪዎች እና ironsmiths – ብረት የሚቀርፁ ከሙያቸው የተነሳ የተወገዙ የማህበረሰብ ክፍሎች ናቸው።

🎯What is vulnerability?

📝Vulnerability refers to the state of being exposed to physical or emotional injuries.

👉 ይህ ማለት ደግሞ #ተጋላጭነት ማለት ነው። ለአካላዊ ጥቃት ወይም ለውስጣዊ ስሜት ጥቃት መጋለጥ ማለት ነው። በማህበረሰቡ ውስጥ ለአካላዊ ጥቃት የተጋለጡ ይኖራሉ፥ አካላዊ ብቻ ሳይሆን ያ ነገር ስሜታቸውንም ጭምር ይጎዳል እናም ለተለያየ "Psychological trauma🤦‍♀️" ሊዳርጋቸው ይችላል። ለምሳሌ ሴቶች👩 🤰ለፆታዊ ትንኮሳ፣ ለአስገድዶ መድፈር እና ለግዴታ ጋብቻ የተጋለጡበት ብዙ ማህበረሰብ አለ። በተለይም በተወሰኑ የኢትዮጵያ ክፍሎች ገና በደንብ ያላደጉ ልጃገረዶችን ለ "Early marriage" ስለሚጋለጡ፥ በዚያ ውስጥ እርግዝና 🤰👩‍🍼– teenage pregnancy ስለሚከሰት፥ ለተለያዩ በሽታዎች – Fistula ለመሳሰሉ ይጋለጣሉ። ከዚህም (ከፊስቱላ) ህመማቸው የተነሳም ደግሞ ማህበረሰቡ መልሶ ገለልተኛ ወይም "Marginalize" ያደርጋቸዋል። እንዲህ ቀለል አድርገን ስናወራው፥ ስላላየነው ቀላል ሊመስል ይችላል ግን በጣም የሚያም፥ የእህቶቻችን ህልም የሚያጨልም🏴ነገር ነው። እንደነዚህ በማህበረሰቡ ውስጥ ተጋላጭ የሆኑ ሰዎች "Special attention🎯, protection🛡 and Support🤝" ያስፈልጋቸዋል።

🎯What is Minority group?

📝Refers to a small group of people within a community, region, or country. 👉"Minority group" የሚባለው በማህበረሰቡ ውሰጥ ዝቅተኛ ስፍራ የሚሰጠው ፣ በቁጥርም ትንሽ የሆነ የማህበረሰቡ ክፍል ማለት ነው። ብዙ ጊዜ "minority groups" ከብዙሃኑ የማህበረሰቡ ህዝብ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በጎሳ ወይም በቋንቋ ያነሱ ናቸው። ለምሳሌ "Muslim🕌በበዛበት ማህበረሰብ ውስጥ ክርስቲያን Minority group ነው፣ በአሜሪካ ውስጥ ያሉ ጥቋቁር አፍሪካውያንም ✋🏿እዚያ minority group ናቸው። እዚህ ጋር "minority" መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ከዚያ የተነሳ ጭቆና ይደርስባችኃል እንጂ "minority" መሆናቸው ችግር ኖሮበት አይደለም። ግልፅ ነዋ🤌

👉እሺ አሁን ወደ "Marginalization" እንመለስና አንድ የማህበረሰቡ አካል የሆነ ሰው በምን ምክንያቶች ከማህበረሰቡ ሊወገዝ ይችላል የሚለውን እንመልከት። There are different forms of marginalization. 📌Gender-based marginalization 📌Occupational " " 📌Age-based " "

🎯Gender-based marginalization

ልብ በሉ! "sex- based" አይደለም። ምክንያቱም "sex" ከፆታ ወይም ከባዮሎጂካዊ ሁኔታ ጋር የተገናኘ ነው። "Gender" ግን ወንዶች እንደ ወንድ፥ ሴቶችም እንደ ሴት በማህረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ድርሻ ያመለክታል። "Gender" ከፆታ ይልቅ ከባህልና ማህበረሰብ ጋር ይገናኛል። ለምሳሌ ሴትን በማህረሰቡ ውስጥ በሆነ ነገር ላይ ገለልተኛ ቢያረጉዋት ፆታዋ ሴት ስለሆነ ሳይሆን የዚያ ማህበረሰብ ባህል የሰዎቹን አይምሮ እንደዛ እንዲደረገ ስለተቆጣጠረው ነው።

📑Gender based marginalization Is discrimination on a group of people based on their gender. It is closely related to gender inequality. 👉For Example, The enrollment of girls in higher education🧒👩 is much lower than that of boys. Women do not enjoy equal employment opportunities.

👉Women👩 and girls👱‍♀️ are vulnerable to gender-based violence Such as rape, early marriage, harmful traditional practices (female genital cutting).

እንደምታውቅት አንድ አንድ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ "Female Genital Mutilation or Cutting - FGM/C" - የሴት ልጅ ግርዛት እንደ መልካም ነገር ነው የሚያየው🙈 ምክንያታቸውም ያልተገረዘች ሴት አትታዘዝም፣ እቃ ትሰብራለች፣ ጋብቻ

ላልተገረዘች ሴት Stable ወይም ምቹና ቀጣይነት ያለው አይሆንም፣ የሴት ልጅ ግርዛት የመንፃቷ ምልክት ነው። ይህ ሁሉ ምክንያት ግን ተራ ነው።😳 ባይሆን "Female Genital Cutting" ምን ምን እንደሚያስከትል ባይሎጂው የሚነግረንን ተመልከቱ👇 ።

"Severe bleeding, Infections, Pain during Sexual intercourse, Delivery complications, and Fistula, Psychological trauma."😭

🙌ስለ ሴት ልጅ ግርዛት በሀገራችን ኢትዮጵያ እንዲሁም በአፍሪካ የቀመጠውን ጥናት ከሞጁሉ ላይ መመልከት ትችላላችሁ። አሁን ላይ ዳታውን መሸምደድም ጠቃሚ አይደለም። ፈተና ላይም አይመጣም።

☝️ከላይ በጥቂቱ የተዘረዘሩት የሴት ልጅን ግርዛት የሚያበረታቱ ማህበረሰብ ውስጥ ያንን ባህል እንዲያስቀጥሉ "Major Factors" የተባሉት በሞጁሉ ላይ በዚህ👇 መልኩ ተቀምጧል።

1 – Belief in Impurity – ካልተገረዘች እንደረከሰች ወይም ንፁህ እንዳልሆነች ስለምትቆጠር፥ ያ ብቻ አይደለም ከእሷ ጋር የሚተኛን ወንድ ሁሉ እንደምታረክስ ነው የሚወሰደው። ስለዚህ በዚህ ምክንያት እሷም ያገባትም ወንድ ከማህበረሰቡ ገለልተኛ ይሆናሉ።

2 – Discouraging Promiscuity – መገረዛቸው አንድም ጥቅሙ ከብዙ ወንዶች ጋር ለወሲባዊ ምኞት ያላቸውን ፍላጎት ይቀንሳል። "Promiscuity" የሚለው ቃል ብዙ የ "sex" ጓደኛ👫 ♂ ያለውን ሰው ነው የሚያመለክተው። ስለዚህ በእነዚህ ማህበረሰብ አስተሳሰብ ሴቷ ከተገረዘች ብዙ እንዳትመኝ ያደርጋታል፥ ይህንን የ "promiscuity" ባህሪ ይቀንሳል ወይም discourage ያደርጋል። ጋብቻዋም "stable" " እንዲሆን ያደርጋል።

3 – Preserving Virginity – እንደምታውቁ በብዙ የሀገራችን ባህል ለድንግልና የሚሰጠው ቦታ ትልቅ ነው። ከዚህም የተነሳ የሴት ልጅ ግርዛት አንዱ ጥቅም ሊሆን ይችላል ብለው የሚያምኑት "ድንግልናዋን እስከ ጋብቻ ድረስ ማቆየት" ነው። ለዚህም TYPE III FGM/C ወይም በሌላ ስሙ "Infibulation" የሚባለው የግርዛት አይነት ይጠቅማል።🙆 ♂

4 – Fear of ill–manner – ከላይ በዳሰሳ እንዳየነው "ሴት ልጅ ካልተገረዘች እንደሚገባ አትታዘዝም ወይም ill–mannered ትሆናለች ማለትም "having bad manners🤷 ♀ – መጥፎ ባህሪዎች ይኖሩዋታል።" ማለት ነው። እናም ያንን ፍራቻ ግርዛት ያካሄዳሉ።

5 – Social Sanctions – ግርዛትን እምቢ ማለት የማህበረሰቡን ህግ እንደሚተላለፍ ወይም የዚያን ማህበረሰብ ቅድስና

– sanction እንደማቆሸሽ ነው የሚወሰደው፥ ስለዚህ የልጅቷ ቤተሰቦች ገለልተኛ ከመደረጋቸውም ባሻገር የማህረሰቡን ባህል ስለተላለፉ ይቀጣሉ። እናም ቤተሰቦች ያንን ፍራቻ ሴት ልጆቻቸውን ለግርዛት አሳልፈው ይሰጣሉ።

🎯Marginalized Occupational Groups

📑The most marginalized occupational groups in many parts of Ethiopia are: tanners [ቆዳ የሚፍቁ – ከቆዳው ላይ የተለያዩ የ "leather" ምርት የሚሰሩ], potters [ጡብ ሰሪዎች – ለእህልና ለመጠጥ የሚሆኑ እቃዎችን የሚሰሩ], weavers [ሸማኔዎች – የተለያየ ድንቅ አልባሳት የሚሰሩ] and ironsmiths[ብረት የሚቀርፁ – የእርሻ መሳሪያዎችን እና የመሳሰሉ ብረቶችን]።

👉በእነዚህ የስራ ዘርፍ የተሰማሩ ሰዎች ፥ ላሉበት ማህበረሰብ በሙያቸው ብዙ ያበረከቱ ቢሆንም እንደ ጠንቋይ🧟♀️😁(Impure – እንዳልነፁ) ይታዩ ስለነበር ከማህበረሰቡ ተገለው "Marginalized ሆነው" ነበር። በእነዚህ ሙያተኞች "craft workers" ላይ የደረሰውን የነፃነት፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ ህብረት፣ የባህል Marginalization ከታች በቴብል ተቀምጧል፥ እዩት፥ መሸምደድ አይጠበቅባችሁም ስሙ ራሱ እራሱን ስለሚያብራራ።🙌

👉However, Craft-workers [ከላይ የዘረዘርናቸውን ስራ የሚሰሩ] in Ethiopia produce several articles such as traditional hand-woven clothes, household utensils, and farm tools. ይህን ያክል ጥቅም እያላቸው ማህበረሰቡ ግን አውግዞአቸው ነበር። እንደውም የሆነ እውነተኛ ታሪክ አለ፥ "መሬት ጠፍጣፋ አይደለችም፥ ክብ ናት።" የሚል Theory ያመጣውን ሰውዬ ማህበረሰቡ ሰቅለውት ነበር የገደሉት😭 ምንጭ: ጎግል

🎯Age-based Vulnerability

📑Age based Vulnerability is susceptibility of people, especially children and older people, to different forms of attacks, physical injuries and emotional harms.

👉For example, children and older people (people aged 60 and above) are exposed to various forms of attack in the society due to their age. 👆ከላይ እንዳየነው "Child/early marriage" እዚህ ስር ማንሳት እንችላለን። ሴቶች በጊዜ ካላገቡ "ቆሞ ቀር" ስለሚባሉ እና ቤተሰብም ቶሎ እንዲያገቡ ስለሚነዘንዟቸው ሴት👱♀️ እህቶቻችን😁 ለዚህ ይዳረጋሉ። ያ ብቻም ሳይሆን ለምሳሌ እድሜው የሄደ ያላገባ ጎልማሳ በጣም "አርጅቷል" ተብሎ ስለሚታሰብ ሚስት የማግኘት እድሉ አናሳ ነው😞 ማለትም ከማህበረሰቡ ልጁን የሚድርለት ቤተሰብ ላይገኝ ይችላል። የሚገርማችሁ Early or Child Marriage ሴት ልጆች ጋር ብቻ አይደለም ያለው። ወንዶች ጋርም አለ፥ እኔ እንደዚህ ያጋጠመው የማውቀው ሰው አለ። ቶሎ አግብቶ ቤተሰቡን ወግ ማዕረግ እንዲያሳይ ይገደዳል። ለዚህ ነው "Early

marriage" gender based ብቻ አይደለም፥ "Age-based" ጭምርም ነው። ነገር ግን ሴቶች ልጆች ለ "double marginalization and discrimination because of their gender and age" የተጋለጡ ናቸው። ይቺ ፈተና ላይ አትቀርም፥ ብዙ ጊዜ

ነገር ግን "Early marriage" የሚያስከትለውን ተመልከቱ👇

"It hinders girls chance to education and personal dev't, leads to early pregnancies, Which increases risks of diseases and complications during delivery, fistula, and death of the mother or child."

🎯Religious and Ethnic Minorities

🔹 የአይሁድ ህዝብ - Jewish People በዘራቸው ምክንያት በጣም ብዙ ዋጋ እንደከፈሉ አይረሳም። በ Adolf Hitler ጊዜ ከ 6 million በላይ አይሁዳውያን እንደተገደሉ አይረሳም😢። ይህ የአይሁዳውያን የጅምላ ጭፍጨፋ ወይም ግድያ "Holocaust" በመባል ይታወቃል።

🔹 "Muslim Rohingyas" የተባለ የሙስሊም🕌የሃይማኖት ወገን፥ ከቅርብ አመታት በፊት ከነበሩበት ሀገር ማይናማር በግማሽ ሚልየን የሚቆጠሩት ከሃይማኖታቸው የተነሳ ተፈናቅለው ነበር።

🙌ስለዚህ "Marginalization" Gender-Based, Age-Based, Occupation-Based, Religion-Based, Ethnic-Based ሊሆን እንደሚችል ከላይ በአሪፍ ሁኔታ አይተናል🥰፡ነገር ግን በመጨረሻ አንድ መደምደሚያ ላይ መድረስ እንችላለን👇 ስለ እነዚህ ሁሉ ሰብዓዊ መብት ምንድነው የሚለው:

"All forms of marginalization and discrimination against vulnerable and minority groups contradict the principles of human rights. The major human rights conventions #denounce discrimination against women, children, people with disability, older people and other minority and vulnerable groups."

🙌ቻፕተር 4 በዚህ መልኩ ጨርሰናል፥ የሚቀጥሉ ምዕራፎችን በቀጣይ ጊዜ እንቀጥላለን። መልካም ጊዜ🤗

ለጥያቄና አስተያየት👇👇 @Ucan_Scorebot

Your Success is guaranteed with A+! ®A+ Tutorial Class

#Anthro

📓Course – Anthropology

˜📗CHAPTER 5

📖Identity, Inter–Ethnic Relations and Multiculturalism

📑Ethnic Groups and Ethnic Identity

🎯Ethnic Group

👉ስለ "Ethnic group" Hutchinson👨 ♂ and Smith👴 የተባሉ ሰዎች የሰጡትን ትርጉም እንመለከታለን።
👴 –>ይሄ ኢሞጂ የባርት አደልንዴ ለSmith ለምን አረከው እንዳትሉኝ ደሞ😁 ሰዎች አንድ ጎሳ (ethnic group) ውስጥ ይመደባሉ ለማለት የሚከተሉትን 6 መስፈርቶች አስቀምጠዋል።

1. Common Proper name: የማህበረሰቡን ማንነት የሚገልፅ ስም ሊኖረው ይገባል። ለምሳሌ ጫላና ጄምስ የሚባል ስም ያላቸው ሰዎች አንድ ጎሳ ናቸው ማለት ይከብዳል😁።

2. Common Ancestry: የመጡበት ወይም የተወለዱበት የጥንት ቤተሰብ 👨 👩 👦 አንድ መሆን አለበት። ዘር ማን ዘራቸው በድሮ ጊዜ አብሮ የኖሩ መሆን አለበት።

3. Shared Historical Memories የሆነ ሼር የሚያረጉት ያለፈ ታሪክ ሊኖራቸው ይገባል። ኮሎናይዝ ተደርገው ሊሆን ይችላል ወይ ደግሞ በጦርነት ድል ነስተው ሊሆን ይችላል እና የመሳሰሉት።

4. Common Culture: አንድ የሚጋሩት ባህል ሊኖራቸው ይገባል። በቋንቋ፣ በልማድ አለፍ ሲልም በሀይማኖት።

5. A Link with homeland ከእናት ሀገር ጋር ቁርኝት ያላቸው። በስራ ወይም በትምህርት✍ ሌላ ቦታ ሄደው ይሆናል ነገር ግን ከሀገራቸው (የጥንት ቤተሰቦቻቸው ከኖሩበት) ሀገር ጋር ግንኙነት ያላቸው መሆን አለባቸው።

6. A sense of solidarity: አንዱ ለሌላው የመራራት ፣ የመተሳሰብ፣ የመረዳዳት አይነት ስሜት ሊኖር ይገባል። በእርግጥ እኛ ላለንበት "Ethnic group" ወይም ጎሳ ብቻ ሳይሆን ለሰው ልጅ ሁሉ መራራት አስፈላጊ ነው።

📑Ethnic Identity

📌Ethnic Identity is an affiliatiive construct, where an individual is viewed by themselves and by others as belonging to a particular ethnic or cultural group. በመጀመሪያ የጎሳ ማንነት ወይም "Ethnic Identity" የምንለው "affiliative construct" ነው ስንል ምን ማለታችን ነው❓ በሰዎች መካከል ያለ ህብረት/Association ማለት ነው። ልክ ህንፃ 🏛ከተለያዩ መሳሪያዎች እና ግብዓቶች እንደሚሰራ "Ethnic Identity is affiliative construct" ስንልም ጠንካራ ህብረት እና ትስስር ያላቸው የሰዎች ስብስብ ማለት ነው። ስለዚህ🤌 ሰው እራሱን የየሆነ ጎሳ አባል አድርጎ እራሱን ሲያስብ ወይም ሌሎች ሰዎች ያ ሰው የዚያ ጎሳ አባል እንደሆነ ሲያስቡ "Ethnic Identity – የጎሳ ማንነት" የሚለውን በዚያ መረዳት ይቻላል።

📌Affiliation can be influenced by racial, natal, symbolic and cultural factors. ይህ "Affiliation – በሰዎች መካከል ያለ ህብረት" የምንለው ነገር ከምን ከምን ሊመጣ ይችላል? እናንት ከዶርም እና ክላስ ጓደኞቻችሁ ጋር ጥሩ ጓደኝነት❤️ እና ተግባቦት እንድትፈጥሩ ያደረጋችሁ ነገር ምንድነው? እስኪ ከላይ ያሉትን አንድ በአንድ እንመልከት🤌

📌 Racial factors: involve the use of physiognomic and physical characteristics. ይህ የሰዎች ውጫዊ ባህሪ እንዲሁም ተክለሰውነታቸው (Physical appearance) ተቀራራቢ ወይም ተመሳሳይ ሲሆን እነዚያ ሰዎች ህብረት/Affiliation እንዲፈጥሩ ምክንያት ሊሆን ይችላል። "physiognomic" ማለት የሰዎች ውጫዊ አካል ለምሳሌ አፍንጫቸው፣ አይናቸው፣ የፊት ቅርፅ... እንደማለት ነው። ለምሳሌ እዚህ ሀገር አንዱ ኮሪያዊ የሱን አይን የሚመስል ሌላ ሰው ሲያገኝ ከዚያ ሰው ጋር ለመተዋወቅ ሊጓጓ ይችላል።

📌 Natal factors: refer to "homeland" (ancestral home) or origins of individuals, their parents and kin [ዘመድ]. ይህ ደግሞ የአንዲት እናት ሀገር (homeland) ተወላጅ የሆኑ ሰዎች ህብረት/affiliation እንዲፈጥሩ

ምክንያት ሊሆን ይችላል።

❣️ Symbolic factors: include those factors that typify or exemplify an ethnic group (eg. Holidays, foods, clothing...) ሰው ከራሱ ባህል ጋር የሚመሳሰል እና የሱን አይነት ባህል የሚጋራ ("Share የሚያደርግ") ሰው ሲያገኝ ከዚያ ሰው ጋር ህብረት ለማድረግ ሊነሳሳ ይችላል። ምናልባት ተመሳሳይ አለባበስ ወይም አመጋገብ🫖 ወይም ሌላ ሊሆን ይችላል።

❣️ Cultural factors: encompasses the set of beliefs, moral values, languages, etc. ሰዎች ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ባህል፦ ቋንቋ፣ እሴት፣ ወግ ምናምን ሲኖራቸው ህብረት ለመፍጠር ወይም "Affiliate ለማድረግ " የፈጠኑ ናቸው።

"Ethnic group" ከሚለው ትንሽ ወጣ ብለን ደግሞ "Ethnicity" የሚለውን በግል ብናየው እንዴት እናብራራለን?

📌On the Individual level, ethnicity is a socio-psychological process, which gives individual a sense of belonging and identity. 👉ይህ ትርጉም ሁለት ሀሳብ በውስጡ እንደያዘ ግልፅ ነው። የመጀመሪያው "Social process" የሚል ነው። ከሰዎች ጋር የህብረት ጉዳይ ነው። ምናልባት ከላይ ከዘረዘርናቸው ምክንያቶች አንፃርም ሊሆን ይችላል "Ethnicity" አንድም ከሰዎች ጋር ማህበር (Sociability) የመፍጠር ጉዳይ ነው። ሁለተኛው ደግሞ "Psychological process" የሚል ነው። ይህም ማለት የዚያ ጎሳ አባል እንደሆናችሁ (sense of belongingness) መኖር አለበት።

🙌ስለዚህ "Ethnic Identity" ሁለት ገፅታዎች (aspects) አሉት። Objective (External) aspects and Subjective (Internal) aspects🤝

🪛Objective aspects refer to Observable behavior both cultural and social such as 👉 speaking an ethnic language, practicing ethnic traditions 👉 Participation in ethnic personal networks such as family and relationships 👉 Participation in ethnic institutional organizations, such as belief systems, social organizations, etc.

 ይህ ከላይ "Social process" በሚለው ያየነው ነው። የዚያን ያላችሁበትን ጎሳ/ብሔር ቋንቋ🗣️መናገር መቻል፣ ባህሉን መጋራት🙆‍♀️፣ እንዲሁም የተለያዩ ተሳትፎዎች ማድረግ (participation in ethnic voluntary associations) እና የመሳሰሉት።

✏️Subjective aspects: refer to images, ideas, attitudes and feelings which can be interconnected with the objective aspects. Three types of subjective aspects of identity can include: cognitive, moral and affective domains. ይህ 👇 ደግሞ የሚያመለክተው ለዚያ ላላችሁበት ጎሳ በአይምሮአችሁ ሀሳብ🧠 (cognitively), በምታሳዩት ስነምግባር (moral) እንዲሁም ልብ የሚነካ ነገር ሲያጋጥም (affective) በእነዚህ ሁሉ ሀሳባችሁን ወይም ስሜታችሁን ስትገልፁ የዚያ ጎሳ አባል እንደሆናችሁ (ለዚያ ተቆርቋሪ እንደሆናችሁ የሚያሳይ መሆን አለበት።

📑The Term Itself–Ethnicity

Ethnicity: ይህ ቃል "ዘር"/"ጎሳ" ታዋቂ እየሆነ የመጣው ከ2ኛው የአለም ጦርነት በኃላ ነው። ከዚያ በፊት ግን "tribe" የሚለውን ቃል ነበር ሚጠቀሙት ከዚያ "race" የሚል ቃል መጣ። ይህ ቃል ግን ከ"Nazi ideology – የዘር ጭፍጨፋ"🙈 ጋር ተቀራራቢነት አለው ተብሎ ስለታሰበ "Ethnic" የሚለው ቃል ተወሰደ።

📝According to John Hutchinson and Anthony Smith the term "ethnicity" is appearing in the Oxford English Dictionary in 1953.

🤔ይሄ "Ethnicity" የሚለው ቃል "Ethnic" ከሚለው ጋር ተያያዥነት ያለው ቃል ነው። "Ethnic" የሚለው ደግሞ "Ethnos" ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ነው። "Ethnos" የሚለው ደግሞ "Ethnikos" ከሚል የLatin Word የመጣ ነው🙈 ቋንቋዎቹ መኮራረጅ አበዙ አ😂

"Ethnicity ← Ethnic ← Ethnos ← Ethnikos"

📌"Ethnikos" means a group of people bound together by the same manners, customs or other distinctive features. ይህ ማለት ደግሞ ተመሳሳይ ባህል፣ ወግ እና ቋንቋ ያላቸው ሰዎች ስብስብ ነው።

📌"Ethnos" refers to a collectivity of humans lived and acted together– Which is typically translated today as 'Nation – ብሔር'.

📑ነገር ግን ግሪኮች ይህን ቃል ("ኢትኖስ–Ethnos") ይጠቀሙ የነበሩት በእነሱ መካከል የሚኖሩ "Non–Hellenic,

Non-Greek- በትውልድ ግሪክ ያልሆኑ ሰዎችን ለመግለፅ ነበር🙈። በጥንት ዘመን ግሪኮች "Hellenic" ተብለው ይጠሩ ነበር ይህ ቃል "Hellazein" ከሚለው ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም "የግሪክን ቋንቋ መናገር ወይም ከግሪኮች ጋር አንድ ላይ መመደብ" ማለት ነው።

📑"North American" ደግሞ ይህን ቃል ይጠቀሙ የነበረው በሀገራቸው ይኖሩ ለነበሩ "Minority groups (Jews, Italians, Africans...)" ነበር። ከዚያም በአውሮፓ ባህል ውስጥም ይህ "Ethnic" የሚለውን ስያሜ ይጠቀሙ የነበሩት በጊዜው ለነበሩት 2nd Class Peoples ወይም non-citizend ለነበሩት "Immigrant Minority ነበር - i.e Pakistani, West Indian, Sri Lankan, etc." አውሮፓውያን ግን ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በፊት "Ethnic group" የሚለውን ለራሳቸው ነበር የሚጠቀሙት፥ ቃሉም "nationhood - የአንድ ብሔር ህዝብ" ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይነት ነበረው።

👉በመቀጠል "Jack David Eller"👨 ♂ የተባለው ሰው ደግሞ "Ethnicity is Vague (እንዲህ ነው ብለን ለማብራራት የሚከብድ- አንፃራዊ የሆነ ነው), elusive (ለመግለፅ አስቸጋሪ), vast (በጣም ሰፊ)" ነው ብሎ ገልፆታል።

ስለዚህ "Ethnicity" ምንድነው? ምንስ አይደለም 🤷

📑Conceptualizing Ethnicity

"Ethnicity - ጎሳ" ምን እንደሆነ እንዲሁም ምን እንዳልሆነ በግልፅ ማስቀመጥ አስፈላጊ ነው። ካለፉት የአንትሮፖሎጂ አባቶች ውስጥ ደግሞ ከ "Max Weber" በቀር ብዙ ትኩረት ሰጥቶት ያጠናው ሰው የለም።

🤦 None of the founding fathers of anthropology and sociology - with the partial exception of Max Weber granted ethnicity much attention. ይህ "Max Weber"👨 🙉የተባለው ታዋቂው ሶሾሎጂስት ለEnthnicity እንዲህ ሲል Definition ሰጠው፦

🙌"Ethnic group is based on the belief in common descent shared by its descent, extending beyond kinship, Political solidarity with other groups and common customs, language, religion, values, morality, and etiquette[ስነ ምግባር]." 📑አያቹ አ Ethnic group/ጎሳ/ ዘር የሚባለው ነገር "ሰዎች ከስጋ ዝምድናቸውም አልፎ ከተመሳሳይ ዘር ማንዘር (ancestry) እንደመጡ ሲያስቡ፣ የሚያደርጉት ፖለቲካዊ ህብረት ሲገናኝ [በራሳቸው ቋንቋ ሲግባቡ፣ የራሳቸውን መንግስት ወይም አስተዳደር ሲመሰርቱ]፣ ተመሳሳይ እሴት እና ወግ ሲኖራቸው አንድ "ዘር" እንደሆኑ አድርገው ነው #የሚያምኑት። 🤦 In other words, ethnic groups are those human groups that entertain a subjective belief in their common descent because of similarities or physical type or of customs or both, or because of memories of colonization and migration. 🙌ወይም ደግሞ ተመሳሳይ የቆዳ ቀለም

(Physical) ወይም ተመሳሳይ እሴት/ባህል ሲኖራቸው ወይም የሚመሳሰል ታሪክ/ትውስታ ሲኖራቸው (like Colonize ተደርገው ወይም ተሰደው ከሆነ) አንድ ዘር እንደሆኑ ያስባሉ። ስለዚህ እንደ "Weber👨 🦳" አስተሳሰብ ዘር #የእምነትን ጉዳይ እንጂ (ሰዎች አንድ ዘር ነን ብለው ወይ ያምናሉ ወይ አያምኑም) እንጂ የስጋ ዝምድና ኖረ አልኖረ🤷♂️ እሱ ችግር አይደለም።

📝The next great contributer to our understanding of ethnicity is anthropologist, named Frederik Barth👴.

Barth began with what actors believe or think: ascriptions and self-ascriptions. ልክ በፊልም አለም የሆነ ሰው ማለትም ተዋናይ👤 አንድን ገፀ-ባህሪ ያንን ሰው መስሎ እንዲጫወት ሲሰጠው ማለት ነው። እናም "Ascription" ስንል አንድን ሰው ካለው የኃላ ታሪክ ተነስተን ስንገልፀው (ያ ሰው ሊቆጣጠረው የማይችል ለምሳሌ የተወለደበት ቤተሰብ፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት እና የመሳሰሉት) ሁላችንም ስንወለድ እንዚህን ነገሮች እራሳችን መርጠን አይደለም። ነገር ግን ስናድግ ማህበረሰቡ ወይም ሰዎች አንተ የእንትና ዘር ነህ እንባላለን፥ ከላይ ከዘረዘርናቸው ነገሮች ተነስተው።

🙌ልክ በፊልሙ አለም አንተ ይህንን ገፀ ባህሪ ትጫወታለህ እኔ ደግሞ ያንን ተብለው እንደሚከፋፈሉ፥ በማህበረሰብም አንተ ያ ዘር እኔ ደግሞ ያ ነኝ እያሉ አንዱ ሌላው ላይ የዘር ስም የመለጣጠፍ ጉዳይ ነው ይለናል Barth.

📝A categorical ascription is an ethnic ascription when it classifies a person in terms of his basic, most general identity, presumptively determined by his origin and background. ስለዚህ "Categorical Ascription" የሚባለውም አንድን ሰው ከማንነቱ፣ ከBackgroundኡ፣ ከአመጣጡ ተነስተን በጎሳ ስንከፍለው ወይም ስንመድበው ማለት ነው።

🎯Barth focused not upon the cultural characteristics of ethnic groups but upon relationships of cultural differentiation, and specifically upon contact between collectivities thus differentiated, 'us' and 'them'. ቅድም የነ ቄበርን አመለካከት ስናይ ትኩረት ያደረገው "ሰዎቹ የሚገኙበት ባህል ገፅታ ማለትም ተመሳሳይ ቋንቋና እሴት ምናምን ስላላቸው አንድ ላይ መደብናቸው" በባርት👴 አመለካከት ግን እንደዛ አይደለም። ቅድም የፊልም ገፀ-ባህሪ ምሳሌ እንዳየነው "እናንት እንደዚህ እኛ ደግሞ እንደዚያ, አንተ እንዲህ አንቺ እንዲያ" የሚል ነው። የሰዎቹ የባህል ልዩነት ህብረት ላይ ነው ትኩረቱ🙌።

🎯The cultural contents of ethnic dichotomies would seem analytically to be of two orders:
👇የአንድን ብሔር የባህል ይዘት በሁለት መንገድ ነው የምንመለከተው፦

👆Overt [ውጫዊ] signals or Signs

📌The diacritical features that people look for and exhibit to show identity, often such features as dress, language, house-form, or general style of life. ይህኛው የሰዎችን ማንነት የሚገልፁ አለባበስ፣ ቋንቋን... የሚያመለክት ነው። ✔"Diacritical" የምትለዋ ቃል ግራ እንዳይገባችሁ "የሆነ መልዕክት የሚያስተላልፍ ምልክት ማለት ነው።"

👆Basic value orientations

📌The standards of morality and excellence by which performance is judged. ይህ ደግሞ የሰውን አስተሳሰብ🧠፣ ሞራል (ስነ ምግባር) የሚገልፅ ነው። ስለዚህ ባህል ከላይ ያየናቸውን ሁለት ነገሮች በውስጡ ይዟል።

እቺን ያዟት🗞️In its most general notion, for Barth, ethnicity is seen as a "Social Organization of Cultural Difference". ከላይ በስፋት ያየነው የባርት👴 ሀሳብ ሲጠቀለል "የ ባህሎች ልዩነት ማህበራዊ ተቋም" ማለት ነው። ተቋም – ያልነው በአጠቃላይ በፊልሙ ውስጥ የተካተቱ ሲሆን የባህል ልዩነት ያልነው ደግሞ – በተቋሙ (በፊልሙ) ውስጥ የሚገኙ ሰዎች የተለያየ ገፀ-ባህሪ መጫወታቸውን የሚያመለክት ነው።

📌ከBarth በፊት Cultural Difference "Inside out – ከውስጥ ወደ ውጪ" ነበር የሚብራራው፣ ማለትም አንድ ሰው የየሆነን ባህል ገፅታ (ቋንቋውን፣ አለባበሱን...) Possess ካደረገ ወይም የራሱ ካረገ– ከተለሚመደው በኃላ ነው በህብረተሰቡ መኃል ያ ሰው ያንን ባህል እንደሚከተል የሚታወቀው። ስለዚህ እዚህጋ ትኩረቱ #ባህል ላይ ነው። ለምሳሌ በጥንት ዘመን ብዙ የባህል ክፍፍል ስላልነበረ አንድ ሰው የዚህን ብሔር ባህል ካልተከተለ "በቃ ያ ብሔር ነው።" ተብሎ ይደመደማል። የወላይታን ባህል ካልተከተለ በቃ እሱ ብሔሩ ጋሞ ነው ይባላል። አፋን ኦሮሞ ቋንቋ የማይችል ከሆነ 'በቃ እሱ አማራ ነው።" አይነት ነገር። ተው ተው! ከፖለቲካጋ አታነካኩኝ😁

📌ነገር ግን Barth, ይህንን ወደ "Outside in" ቀየረው፣ ማለትም ከህብረተሰቡ ጋር ያለን Social Interaction ነው ባህል እንዲኖረን የሚያደርገው። "Ethnicity" የህብረት [relationship] ጉዳይ እንጂ የተወሰነ ቡድን ንብረት ("Property of a group") አይደለም። አንድ ሰው ወደ አንድ ማህበረሰብ ሄዶ ከማህበረሰቡ ጋር ህብረት ከፈጠረ፣ አብሮ መኖር፣ አብሮ መስራት፣ መብላት፣ መጠጣት እና ሌሎች ያ ሰው የዚያ ብሔር አካል ሊሆን ይችላል። ባርት ደግሞ ትኩረቱ #Relationship ወይም ህብረት ላይ ነው።

ስለዚህ ባርት "Ethnicity" የተባለውን ነገር ከቋንቋ፣ ከወግ ምናምን ጋር አያይዘውም ይልቁኑ ሰዎቹ የሚያደርጉት ቁረኝት – Interaction ነው። በዚያ የ "Interaction Process" መሃል እነዚህ "Interact የሚያደርጉ ሰዎች/ማህበረሰብ

ከሌሎች ህዝቦች ጋር "Cultural Differences" ሊፈጥሩ ይችላሉ ነው የሚለው እንዴት ድንቅ አመለካከት ነው።

🙌Furthermore, Barth's research established a foundation for understanding ethnicity in universalist rather than in particularist term. Since culture and social groups emerge only through interaction with others, then ethnicity cannot be restricted to minority or particular groups only.

ለዛሬ እዚህ ላይ ይብቃን🙌 መልካም ጊዜ🤗

ለጥያቄና አስተያይት👇 @Ucan_Scorebot

All rights reserved! ©A+ Tutorial Class

˜📗Anthropology

´📘Chapter Five – Continued

📑Theories of Ethnicity

"Ethnicity ወይም ብሔር/ጎሳ የተባለው ነገር እንዴት ተመሰረተ? ከየት መጣ? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እስካሁን ሶስት ቲዎሪዎች/ሀሳቦች ተመስርቷል፥ ቀጥለን እነሱን እንመለከታለን😙

1🟦The Primordial Model of Ethnicity

👉Primordialism is an "objectivist or essentialist theory" which argues, that "ultimately there is some real, tangible, foundation for ethnic identification." የዚህ ቲዎሪ ዋና ፅንሰ ሀሳብ "Ethnicity ባዮሎጂካል በሆነ መንገድ በዘር የሚተላለፍ ነው።" የሚል ነው። ሰው ልክ እንደተወለደ የዚያ ብሔር አንድ አባል ወይም አካል ተደርጎ ይቆጠራል። ከቲዎሪው ስም ራሱ መረዳት እንደምትችሉት🤔"Primordial ማለት እራሱ "ከመጀመሪያ ጀምሮ ያለ ወይም የተፈጠረ" እንደማለት ነው። እናም የአንድ ሰው የብሔር መገለጫ [Ethnic Identification] ያ ሰው ከመጀመሪያው

ጀምሮ– Primordial (ሲወለድ👦) ከብሔሩ ጋር የነበረው ቁርኝት/Attachment ላይ ነው የተመሰረተው።

"Essentialist/ Objectivist Theory ነው" ስንል ደግሞ ምን ማለታችን ነው🤷‍♂️ 👉የትኛውም የሰው ልጅ ሊታይ፣ ሊጨበጥ የሚችል ማለትም ልንክደው የማንችለው ማንነት አለው ማለታችን ነው።

 In an essentialist view, identity consists of an inner core, which emerges at birth or childhood and unfolds during the course of life, but basically remains the same.

📑Moreover, Smith👴 indicated that, 'primordialism' makes two distnict claims:

🧨Firstly, ethnicity and ethnic attachment is "natural and innate" which would never change over time. "ብሔር ወይም ጎሳ የምንለው ነገር ተፈጥሯዊ (natural) እና በመወለድ (innate) የሚገኝ ነው፥ ተፈጥሯዊ ከሆነ ደግሞ ማንም ይህን ሊነጥቀንም ሆነ ሌላ ሊሰጠን አይችልም🤦‍♂️" የሚል ሀሳብ ነው ያለው።

🧨Secondly, it is "ancient and perennial", fixed, permanent and primarily ascribed through birth. ይህ ሁለተኛው የዚህ (Primordialism Theory) ሀሳብ ደግሞ "Ethnicity የጥንት (ancient) እና መጀመሪያው እስከማይታወቅ ድረስ በጣም የቆየ (perennial) ነው የሚል ነው። ይህም ማለት ሰው የመጀመሪያ የዘር ሀረጉን ለማወቅ ይከብዷል። ነገር ግን ጎሳቸውን በመዋለድ ያስቀጥላሉ፥ አይቋረጥም (Permanent – ቋሚ ነው) የሚል ሀሳብ ነው ያለው።

📌ይህ ቲዎሪ ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተቀባይነቱ ብዙም አይደለም። ምክንያቱም አሁን በዘመናዊው አስተሳሰብ "Ethnicity'ም ሆነ Race/ዘር Social Construction ነው።" ተብሎ ስለሚታሰብ። ማለትም በውልደት👶 ሳይሆን ሰዎች እራሳቸው ተሰብስበው የገነቡት ስርዓት ነው የሚል ሀሳብ የተሻለ ተቀባይነት ስላለው።

2🟦Instrunmentalist [Situational] Theory of Ethnicity

📌This theory views ethnicity as something that can be changed, constructed or even manipulated to gain specific political or economic ends.

"Ethnicity" ለተለያየ የፖለቲካ ወይ የኢኮኖሚ አላማ ሲባል ሊገነባ፣ ሊቀየር ሊፈርስም ይችላል። ነገር ግን የዚህ ቲዎሪ ዋና ሀሳብ ምንድነው "ብሔርን እንደ "Instrunment" ነው የሚመለከተው። ሰዎች ለተለያዩ አላማዎች ስልጣን ላይ ለመውጣት ወይ ለሌላ ነገር እንደ መሳሪያ የሚጠቀሙበት ነው ብሎ ያብራራዋል። ለዚህ ደግሞ "Chinese Ethnicity" ምሳሌ መውሰድ ይቻላል። በታይዋን ሸዎች (Taewanese people እና ሌሎች የቻይና ብሔሮች መካከል ያለው አለመስማማት) ድሮ ሰዎች ለፖለቲካ አላማ😤 የፈጠሩት ነገር እንደሆነ ነው ታሪክ የሚያሳየው።

🔖According to instrumentalism, ethnicity is a tool used by people to achieve their goals because people who share ascriptive characteristics can be effectively organized and mobilized in order to influence public policies.

3🟦Social Constructivist Theory of Ethnicity

📌Ethnicity is something that is being negotiated and constructed in everyday living. Therefore, Ethnicity is situational, flexible, variable and changes through time.

ይህ ቲዎሪ ደግሞ "Ethnicity የሚገነባ፣ ሊጨመርበት ሊቀነስበት እንዲሁም ሊሻሻል የሚችል ነገር ነው።" ብሎ ነው የሚያምነው። ለምሳሌ በ1992, ኢንግሊዝ 🇬🇧 ውስጥ ከሚኖረው አጠቃላይ ህዝብ 31% የሚሆነው እራሱን ኢንግሊዛዊ እንደሆነ ነበር የሚያስበው ብዙ አመት ሳይሞላው ይህ ቁጥር ወደ 41% አደገ። የህዝቡ ብዛት አልጨመረ፣ ወይ ደግሞ ሌላ ተዓምር አልተፈጠረም። ነገር ግን ሰዎች "ኢንግሊዛዊ ነን።" እያሉ እራሳቸውን የኢንግሊዝ ብሔር ውስጥ ማካተት ጀመሩ። 🤔እያችሁ አይደል በዚህ ቲዎሪ መሰረት ብሔር በሰዎች እራሳቸው ሊገነባ የሚችል ነገር እንደሆነ መረዳት እንችላለን።

🔖This theory has subjectivist stance, which sees ethnicity as basically a socio-psychological [ከላይ ያየነው] reality of individual or a matter of perception of "Us" and "Them". ▯ "subjectivist ነው።" ስንል በግለሰቡ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ነው የሚገልፀው። ያ ግለሰብ እራሱን የዚያ ብሔር አካል አድርጎ ሲቆጥር ነው። እንደ Primordialism "Objectivism – የተረጋገጠና በውልደት የሚታወቅ ብሔር" አይደለም! ልብ ይበሉ 🫀

🙌እዚህጋም አንድ ልንወስደው የምንችለው ምሳሌ አለ። የእነ "Huttu እና Tutsi" የዘር ጭፍጨፋ▯ ታሪክ። እነዚህ ሁለቱ ብሔሮች መጀመሪያም የነበሩ ሳይሆን ቤልጂየም 🇧🇪 ሩዋንዳን 🇷🇼ከወረረች በኃላ የተፈጠረ ነው። ቤልጂየም ለፖለቲካ አላማ ስትል እነዚህን የአንድ ሀገር ሰዎች መካከል የብሔር ክፍፍል እንዲከሰት አደረገች። ከዚያም ሰዎቹ ተከፋፈሉና "Us – እኛ" እና "Them – እነሱ የሚል" ሀሳብ🧠(perception) በውስጣቸው አደረ። አያችሁ አይደል ብሔር እንደ "primordialist👶" ሳይሆን "construct" ሊደረግ እንደሚችል ይህ ቲዎሪ ይነግረናል።

ይህም ቲዎሪ ግን ትንሽ ችግር አለበት ለምሳሌ አንዳንድ ጎሳዎች አሉ፦ ፖለቲካ ሳይገድባቸው፣ ኢኮኖሚ ሳይገድባቸው ብዙ ዘመን የቆዩ፥ ቁርኝታቸው❤️ የስጋ ዝምድና እስኪመስል ድረስ የጠነከረ። ይህ ቲዎሪ ደግሞ ብሔር እንደየ አላማው ሊገነባም ሊፈርስም የሚችል ነው ስለሚል ይህ ቲዎሪ ለእንደዚህ አሁን በምሳሌ ላየነው አይነት ሊሆን አይችልም።

እነዚህን ይመስላሉ እንግዲህ። ግልፅ ይመስሉኛል። ከታች በፎቶ ላይ በቴብል በጣም በአጭሩ ተቀምጧል። በስፋት ማየት ለምትፈልጉ ለአሳይመንት📜 ወይም ለፕረሰንቴሽን ካስፈለጋችሁ ደግሞ አሪፍ Pdf ከታች ለቅቄላችኃለሁ🤗፡

©A+ Tutorial Class

📑Multiculturalism: Definition and Theories 🎯Multiculturalism can be defined as the way in which a given society engages with cultural diversity. 👉የአማርኛ አቻ ቃል ያለው አይመስለኝም። ግን "ሕብረ-ባህል" የሚል ስያሜ ሰጥችዋለሁ😄። በቀላሉ ልትረዱ እንደምትችሉት አንድ ህብረተሰብ የተለያየ ባህል በውሰጡ የሚይዝበት መንገድ ማለት ነው። እሩቅ ሳንሄድ በዚሁ በኢትዮጵያ, አዲስ አበባን ብንወስድ የተለያዩ ባህል ያላቸው ሰዎች እንደ አንድ ህብረተሰብ የሚኖሩበት ነው።

🎯Sociologically, multiculturalism assumes that society as a whole benefits from increased diversity through the harmonious coexistence of different cultures. 👉ደግሞም ይህ "Multiculturalism" ለአጠቃላይ ማህበረሰቡ ይጠቅማል። በመቻቻል፣ በህብረት ሲኖሩ ብዙ ጥቅም ያገኛሉ፥ ጥቅሙን መጨረሻ👇 ላይ አሳጥረን እንመለከተዋለን።

📑Theories of Multiculturalism 🌹 There are two theories or models to conceptualize multiculturalism. These are the “melting pot” and the “salad bowl” theories.

🎯These theories are used to understand how different cultures are integrated into a single society.

👉Multiculturalism እንዴት ሊመሰረት ይችላል የሚለውን ለማየት ሁለት አይነት ቲዎሪዎች አሉ። የእነዚህ ቲዎሪዎች ስም በምሳሌያዊ ቃላት👌 ነው የተሰየመው። ቀጥለን እንመልከተው።🙌

1🟦The Melting Spot Theory : This theory assumes that different immigrant groups will be inclined to

“melt together,” leaving their own individual cultures and subsequently will be fully assimilated into the predominant society and its culture.

👉በመጀመሪያ ለምን እንዲህ እንደተሰየመ እንመልከት! "Melting Spot" ማለት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ኤለመንቶች Melt አድርገው ወይም ቀልጠው Mix የሚያደርጉበት ነጥብ ወይም ቦታ ነው። "Elements iron and carbon are melted together to create a single, stronger metal steel." ልክ እንደዚሁ "Multiculturalism" የተለያየ ባህል ያላቸው ሰዎች ወደ አንድ አከባቢ መጥተው "fully assimilated – ሙሉ በሙሉ ተቀላቅለው" የሚኖሩበት ማህበረሰብ ነው። ለምሳሌ 🇺🇸አሜሪካ የሚኖሩ ሰዎች ከተለያየ ባህል የመጡ ሰዎች ናቸው። እናም ሰዎች ብዙ ጊዜ እዛ ብዙ አመታት ሲኖሩ "Predominant – ቀድሞ በዚያ ማህበረሰብ ውስጥ Dominate ያደረገውን/ የተቆጣጠረውን ባህል ወርሰው ወይም ተቀላቅለው ይኖራሉ እንጂ የራሳቸውን ባህል በዚያ ለማስቀጠል አመቺ አይደለም።

"This simply means heterogeneous cultures will be mixed and become one or create a monoculture." 👉ግን ደግሞ አንዳንድ ምሁራን ይህንን ቲዎሪ የሚነቅፉበት ምክንያት አለ። ሰዎች የራሳቸውን ባህል ትተው ወይም ጥለው ወደ አንድ ባህል እንዲመጡ ስለሚያደርጋቸው፥ ወደፊት Diversity የሚባለው ነገር አይኖርም። ከዚህ የተነሳ ደግሞ ሁሉ ወደ አንድ አገዛዝ የመምጣት እድሉ ሰፊ ስለሆነ ለፖለቲካዊ ግጭት መንስዔ ሊሆን ይችላል ይባላል።

2🟦 The Salad Bowl Theory : This is more of a liberal theory of multiculturalism in comparison to the melting pot theory. The salad bowl theory illustrates a heterogeneous society in which people coexist by retaining at least some of the distinctiveness aspects of their traditional culture. 👉ይህኛውንም የተሰየመበትን ቃል ከማብራራት እንጀምር። ሁላችሁም ማለት በሚቻል ደረጃ አትክልት🍱 በሌላ ስሙ "Salad" በልታችሁ ታውቃላችሁ ብዬ አስባለሁ። የአትክልት ምግብ ከወሰዳችሁ እላዩ ላይ የተለያዩ የአትክልት አይነቶችና ፍራፍሬዎች አሉ፥ ድንች፣ ካሮት፣ ሙዝ፣ ቆስጣና የመሳሰሉት፥ ምግቡ የእነዚህን ሁሉ በአንድ ትሪ የያዘ ነው። የበያይነት ወጥም ብንወስድ ለዚህ ምሳሌ ሊሆን ይችላል።🤌 ይህም ቲዎሪ እንደዚሁ ምሳሌ ነው። ሁሉም በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ይዘው የመጡትን የራሳቸው ባህል ሳይጥሉ አብረው የሚኖሩበት ነው። ለዚህም ነው ከላይ ባለው definition "more of liberal" የሚለው፥ ማለትም ከመጀመሪያው ቲዎሪ አንፃር ይህኛው ነፃነት ያለበት ነው። ሁሉም የራሱን ባህል ይዞ በነፃነት በአንድ አከባቢ የሚኖርበት ነው።

🤚New York City, in the United States, is considered as an example of a salad bowl society. It comprises many unique ethnic communities like “Little India,” “Little Odessa,” and “Chinatown”.

👉ነገር ግን ይህም ቲዎሪ ደካማ ጎን አለው። እሱም በተለያዩ ሰዎች ባህል መሃል "ethnocentrism" ሊፈጠር ይችላል። ማለትም የኔ ይበልጣል፣ የኔ ይሻላል ማለትን ሊያስከትል ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ በአንድነት ሆነው ህብረተሰቡን ለመገንባት አይሰሩም፥ ሁሉም የየራሱ ባህል እድገት ላይ ብቻ ተሳታፊ ሊሆን ይችላል።

🎯The defining characteristics of Multicultural societies are that people of different races, ethnicities, and nationalities living together in the same community. In multicultural communities, people up hold, transfer, cherish, and share their distinctive cultural ways of life, languages, art, traditions, and behaviors.

👉"Multiculturalism" ጥቅም እንዳለው የታወቀ ነው። በተለያዩ ሰዎች እንዲሁም Culture'ኦች መሃል የልምድ፣ የክህሎት፣ የቴክኖሎጂ እና የመሳሰሉት ነገሮች ልውውጥ ስለሚኖር ጥሩ ነው። ከዚያም በተጨማሪ ደግሞ መገለጫዎቹንም (Its Characteristics) ብንመለከት አንድ Multicultural የሆነ ማህበረሰብ የለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችን በውስጡ የያዘ፥ የአኗኗር ዘይቤን፣የቋንቋን እና ባህሎችን የሚጋራ ማህበረሰብ ነው።🙌

ይህ ምዕራፍ ይህን ይመስላል። በቀጣይ ቻፕተር 6 እንመለከታለን። መልካም ጊዜ🤗

ለጥያቄና አስተያይት👇 @ucan_scorebot

All rights reserved! ©A+ Tutorial Class